**ዲላ ዩኒቨርሲቲ**

**የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት**

**የአማርኛ ቋንቋና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል**


# የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በተዘጋጀው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተተኳሪነት

(የአርት ማስተርስ ማሟያ ጥናት)


በአብዮት አራጋው



ሰኔ 2013 ዓ.ም.

ዲላ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል

# የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በተዘጋጀው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተተኳሪነት

በአብዮት አራጋው

አማርኛን በማስተማር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ነጥቦች በከፊል ለማሟላት ለአማርኛ ቋንቋና ስነጽሑፍ ትምህርት ከፍል የቀረበ ጥናት

የጥናቱ አማካሪ

በኢዮብ ቀለመወርቅ (ዶ/ር)

ሰኔ 2013 ዓ.ም.

ዲላ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

ድህኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል

እኛ ከዚህ በታች የፈረምነው "በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአብዮት አራጋው ተዘጋጅቶ አማርኛን በማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ይህ ጥናት ከዩንቨርሲቲው ደንብ ጋር የሚጣጣም እና የአዲስነትና ጥራት ደረጃን የሚያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

አማካሪ----------------------------------------- ፊርማና ቀን-----------------

የውጭ ፈታኝ---------------------------------- ፊርማና ቀን-----------------

የውስጥ ፈታኝ-------------------------------- ፊርማና ቀን-----------------

# ማረጋገጫ

“በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻ” በሚል ርእስ በዲላ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣የአማርኛ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በማስተማር መስክ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት፣ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ ስራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

አብዮት አራጋው

ሰኔ 2013 ዓ/ም

# ምስጋና

ከሁሉ በላይ ይህንን ጥናት አስጀምሮ ላስፈጸመኝለመድኃኔዓለምክብርና ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠልም ከጥናቱ መባቻ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ በስልክና በኢሜይል አድራሻ  በየጊዜው የጥናት ስራዎቼን ቀጣይነትና ወጥነት በመገምገምና በማረጋገጥ ሀሳቡን በማቃናትና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ውድ ጊዜያቸውን በመስጠት፣ ጥናቴ ህይወት እንዲዘራ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተር ኢዮብ ቀለመወርቅከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በጥናቱ ሂደት መረጃዎችን በማጠናክርበት ወቅት የሀሳብ ድጋፍ ላደረጉልኝ ጓደኞቼ ሁሉ ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ማንኛውም የጥናቱን ዝግጅት ሳከናውን በትየባ፣ ቴክኒክና ኤዲት የማድረግን ስራ ላገዘኝ ለውድ ባለቤቴ እና ለውድ ልጆቼ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

## ርዕስገጽ


ማረጋገጫ ..................................................... iii

ምስጋና ..................................................... iv

ማውጫ..................................................... v

የሰንጠረዥማውጫ ..................................................... vii

አጠቃሎ..................................................... viii

ምዕራፍ አንድ..................................................... 1

መግቢያ ..................................................... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..................................................... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..................................................... 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ..................................................... 3

1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ..................................................... 3

1.3.2. የጥናቱንዑሳንዓላማዎች..................................................... 4

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ..................................................... 4

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..................................................... 4

1.6. የጥናቱ ወሰን..................................................... 5

ምዕራፍ ሁለት..................................................... 6

ክለሳ ድርሳናት ..................................................... 6

2.1. የሰዋሰው ምንነት..................................................... 6

2.2. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት..................................................... 8

2.3. በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት..................................................... 9

2.3.1. ተከታታይነት ..................................................... 10

2.3.2. ተለጣጣቂነት..................................................... 10

2.3.3. መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት..................................................... 11

*2.3.4.* ከዝርዝር ወደ አጠቃላይአደረጃጀት ..................................................... 12

2.3.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ..................................................... 12

2.4. በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ..................................................... 12

2.4.1. ግልፅነት ........ 13
2.4.2. ትክክለኛነት ........ 13
2.4.3. ተገቢነት ........ 14
2.4.4. ተመጣጣኝነት ........ 15
2.5. የቋንቋ መርሃ ትምህርት ምንነት ........ 16
2.6. የመርሀ ትምህርት ዓላማ ........ 17
2.7. የመርሀ ትምህርት ጠቀሜታ ........ 17
2.8. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........ 18
2.9. የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት ግንኙነት ........ 19
2.10. የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 20
ምዕራፍ ሶስት ........ 22
የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ........ 22
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 22
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 22
3.3. የመረጃ ምንጭ ........ 23
3.4. የናሙና አመራረጥ ........ 23
3.5. የመረጃ አተናተን ........ 23
ምዕራፍ አራት ........ 24
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........ 24
4.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ገጽታ (ቅኝት) ........ 25
4.2. በ2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ........ 29
4.2.1. ከተከታታይነት አንጻር ........ 29
4.2.2. ተለጣጣቂነት ........ 33
4.2.3. መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት ........ 35
4.2.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንጻር ........ 36
4.2.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር ........ 38
4.3. የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍና ለዚሁ ክፍል ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው መጣጣም፤ ........ 42

4.4. በ2009 ዓ.ም.በታተመው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ... 44
4.4.1. ከግልጽነት አንጻር ... 45
4.4.2. ከትክክለኛነት አንጻር ... 47
4.4.3 ከተገቢነት አንጻር ... 48
4.4.4 ከተመጣጣኝነት አንጻር ... 49
4.5 የውጤት ማብራሪያ ... 51
ምዕራፍ አምስት ... 54
ማጠቃለያና አስተያየት ... 54
5.1. ማጠቃለያ ... 54
5.2. አስተያየት ... 55
ዋቢ ጽሑፎች ... 56

## የሰንጠረዥማውጫ

ሰንጠረዥ 1፤- የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ መረጃ ... 27
ሰንጠረዥ 2፡- የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ መረጃ ... 28
ሰንጠረዥ 3፡- በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚገኙባቸው ሳምንታት የድግግሞሽ መጠን ... 30
ሰንጠረዥ 4 ፡- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ... 41
ሰንጠረዥ 5፡- የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ-መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው መጣጣም ... 43
ሰንጠረዥ 6፤-በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስርጭት ... 49

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ነው። በመሆኑም የመማሪያ መጽሐፉ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በስፋትና በጥልቀት ተፈትሸዋል። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ወሳኝ የናሙና ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል። ጥናቱም ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልትን ተጠቅሟል። ጥናቱ በሰነድ ፍተሻ መረጃዎችን ሰብስቧል።በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በዓይነታዊ ስልት በመጠቀም ተተንትኗል። ማብራሪያም ተደርጎባቸዋል። የጥናቱ ግኝትም በመማሪያ መጽሐፉ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ካነሳቸው የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ አንጻር ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ጥሩ በሚባል አደረጃጀት እንደቀረቡ ተረጋግጣል። ዘጠና ሰባት በመቶ የሚሆነው የሰዋስው ይዘት ከአቀራረብ፣ ከተገቢት፣ ከግልጸኝነት፣ ከትክክለኛነት እና ከተመጣጣኝነት አንጻር እንደ ጠንካራ ጎን የታየ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ግን በምዕራፍና በጊዜ አለመከፋፈሉ እንደ ድክመት ታይቷል። ይህንን መነሻ በማድረግም በጥናቱ መጨረሻ ላይ ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱዳራ

ሰዋስው የቋንቋ መሰረት ከሆነው ድምጽ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ደረጃ ያለውን የቋንቋ የስርአት ጥናት የሚመለከተው ሲሆን በጥናቱም የድምፅ አፈጣጠርና አቀነጃጀት፣ የቃላትና የሐረጋት አመሠራረት፣ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ወዘተ. የስርዓት ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት በሚገባ ተረድተው በትክክለኛ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርጽ፤ ፍቺና አጠቃቀም አስተሳስሮ ማቅረብ እንደሚገባው Larson-Freeman(1986) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ለማቅረብ በመጀመሪያ የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት መሰረት በማድረግ ተገቢ የማስተማር ስነ-ዘዴን መምረጥ እንደሚያስፈልግና የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ የይዘት አመራረጥ፤ አቀራረብና አደረጃጀት መከተልና ከቋንቋው ጋር የሚገናኙ መልመጃዎችንና ተግባራትን በምሳሌዎችና በማብራሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ እንደሚያስፈልግም ያስረዳሉ፡፡

Ur (1988፣ 4-5) በአንድ ቋንቋ የሰዋስው ችሎታ ከሌለና አጠቃቀሙን በአግባቡ ለይተን ካላወቅን የቋንቋ ችሎታችን ደካማ ወይም ጎዶሎ መሆኑእንደማያጠያይቅ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ባየ (2004፣ገጽ 13) ስለ ሰዋስው ምንነት እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> ሰዋስው የሚለው ቃል በግዕዝ መሰላል ማለት ነው፡፡ መሰላል ከአንድ አነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ቀስ በቀስ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ የአማርኛ ሰዋስው ሲባል የአማርኛን ድምፆች አይነት፤ አፈጣጠርና አቀነጃጀት፤ የአማርኛን አመሰራረትና አቀነጃጀት፤ እንዲሁም የሀረጋቱን ዓይነትና አወቃቀር ስርዓት ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ የዕውቀት ዘርፍ ማለት ነው፡፡ ድምጽ ከድምጽ ጋር ተቀናጅቶ ቃልን፤ ቃል ከቃል

ጋር ተጋጥሞ ሀረግን፤ እንዲሁም ሀረግ ከሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገርን ደረጃ በደረጃ የሚፈጥርበትን ስርዓት የሚመለከት ጥበብ ነው።

በተጨማሪም ማረው (2003፣ ገጽ 39) የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የመግባባት ችሎታ ማሳደግ ነው። በመሆኑም የሰዋሰው ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች የሚማሩበትን ቋንቋ አጠቃቀም (ክህሎት) እና ስርጭት ጠንቅቀው ሊያውቁ በሚያስችላቸው መልክ ሊቀርብ እንደሚገባ ገልፀዋል።

ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው ሲሆን ይህም በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፤ ሁለተኛ ቋንቋና የውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው ይጠቁማል።

በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የተማሪውን የቋንቋ ዕውቀት በተሟላ ሁኔታ ማሳደግ የሚችሉና የተማሪዎችን የመግባባት ችሎታ ከፍ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ሊቀረጹ ይገባል። ይህም በተገቢው መንገድ ተዘጋጅቶ በቀረበው የሰዋስው ትምህርት ዓላማና ይዘት መነሻነት ተማሪዎቹ የሰዋስው ዕውቀታቸውን ምን ያህል እንዳዳበሩ ለመመዘን ያግዛል። በዚህም መሰረት የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፍቶቹ ውስጥ በተገቢው መንገድ መቅረብ አለመቅረባቸውን ለማረጋገጥ ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል ሲሉ ይህንንም Dubin and Olshtain (1986፣ 2-3) ይገልፃሉ። በአጠቃላይ ሰዋስውን በተመለከተ ምሁራኑ የሰጡት ሀሳብ ከክሂሎች እኩል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን እና በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥም የተማሪዎችን ችሎታ ከፍ ሊያደርግ በሚችል መልኩ ተደራጅቶ መቅረብ እንዳለበት አመልክተዋል።

በመጨረሻም በዚህ ጥናት በ3ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት አንፃር ምን እንደሚመስል ለመመርመር ይሞከራል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ባየ (2004፣ ገጽ 11) የአማርኛ ሰዋስው በአጭርና ቀላል አቀራረብ መጽሀፉን ለማዘጋጀት ያነሳሳቸውን ምክንያት ሲገልፁ ከዚህ በፊት የተዘጋጁት መጻህፍት በዋናነት የከፍተኛ ተቋማትን የቋንቋ ትምህርት መሰረት በማድረግ ነው። በሁለተኛ እና በአንደኛ ደረጃ ለሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በተለየ አቀራረብ ነው። ሁሉንም ጉዳይ ዳር እስከ ዳር በማቅረብ ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱ ለየደረጃው ጠቃሚ የሚሆነውን ብቻ በመለየትና ቀለል እያደረጉ ደረጃ በደረጃ በማቅረብ ነው ሲሉ አስቀምጠዋል።

በመሆኑም ከላይ ከምሁሩ የተነሳው ሀሳብ አጥኚዋ በቅርበት ከምታገኛቸው ተማሪዎችና ባደረገችው ጥናታዊ ጽሑፎች ዳሰሳ የሚስተዋል ዋነኛ ችግር በመሆኑ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በመሆናቸው ከታች ጀምረው በየደረጃው ስለ ሰዋስው ትምህርት እያወቁ እንዲመጡ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ለሰዋስው ዕውቀት የሚሆን ይዘት ተካቷል? ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅቷል? በመርሃ ትምህርት ውስጥ ለሰዋስው ይዘት የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው? የሚለውን ለማወቅ አጥኚዋ ጉጉት ስላደረባት ነው። ስለሆነም የሰዋስው ይዘት አደረጃጀቱ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የተደራጁ ናቸውን? የሚለውን ለመለየትና ጥንካሬና ድክመቱን ለመፈተሽ አጥኚዋ ተነሳስታለች። በተጨማሪም የመማሪያ መጽሀፍ ዝግጅት በአንድ ወቅት ብቻ ተዘጋጅቶ የሚያበቃ ተግባር አይደለም። ስለዚህ የተለያዩ ምሁራን እየተፈራረቁ ስለሚያዘጋጁ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሰዋስው ይዘት አደረጃጀትን በሚመለከት በመርሃ ትምህርት አንፃር የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል እንደሆነና በተሰጠው ትኩረት አንፃር መደራጀታቸውን ጭምር ለማየት ነው። ምክንያቱም የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት በአግባቡና ግልጽ በሆነ መልኩ የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን መያዝ ስለሚኖርባቸው ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በ 2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ይሆናል። ከዚህ ዋና ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ይኖሩታል።

### 1.3.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች

ይህ ጥናት ከላይ የተገለፀውን የጥናቱን ዓብይ ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ንዑሳን ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መፈተሽ፤
3. በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር መገምገም፤

### 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በ 2009 ዓ.ም.በታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ይሆናል።

1. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል?
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል?
3. በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር ምን ይመስላል? የሚለውን በመፈተሽ ምላሽ ያገኛል ተብሎ ይታሰባል።

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው። በመሆኑም በታላሚው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል።

ሀ. በሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ረገድ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳየት የሚሻሻልበትን አቅጣጫ ለቋንቋ መማሪያ መጻህፍ አዘጋጆች ይጠቁማል።

**ለ.** በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ምን ዓይነት ገጽታ እንዳለው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ሐ. የቋንቋ መምህራን ይህን ጥናት የማየት ዕድል ቢገጥማቸው የሚያስተምሩባቸው መጻህፍት ሰዋስዋዊ ይዘታቸውን ለመገምገም የሚያስችላቸውን መነሻ ሀሳብ ሊያገኙባቸው ይችላሉ ተብሎ ይታመናል የሚሉት ናቸው፡፤

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በ 2009 ዓ.ም. የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀት እና አቀራረብ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥም በመማሪያ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ከድምፅ ጀምሮ እስከ ዓረፍተነገር ያሉትን በማየት ይሆናል፡፡ ከሰዋስው ይዘት ውጭ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሌሎች ይዘቶችን ጥናቱ አያካትትም፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው ለዚህ ጥናት በተመረጠው በ2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና ለደረጃው የተዘጋጀው የመርሀ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርትይዘቶችአደረጃጀት እና አቀራረብ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከላይ በተጠቀሰው ይዘት ዙሪያ ብቻ የሚያጠነጥን ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ከጥናቱ ዓላማ አንጻር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ በመጀመሪያ የመርሀ ትምህርት ምንነትን የሚዳስስ ክፍል ሲሆን፤ ሁለተኛው ክፍል የሰዋስው ምንነትን እና ተዛማጅ ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሁፎች በአጭሩ የሚቃኝ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ምዕራፍ ከላይ ያነሳናቸውን ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚዳስስ ሲሆን እያንዳንዱን ክፍል ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.1. የሰዋሰው ምንነት

የሰዋስው ምንነት በተመለከተ የመስኩ ባለሙያዎች በተለያየ መንገድ የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ እንደየምሁራኑ እይታ ምንነቱ ስለሚለያይ እሰከ አሁን ድረስ ስለሰዋስው ምንነት ወጥ የሆነ ብያኔ የለም፡፡ ስለ ሰዋስው ሲነሳ ስለ ቋንቋ ማንሳቱ ግድ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ሰዋስውን ከቋንቋ ለይተን ማየቱ የማይታሰብ ነገር በመሆኑ ነው፡፡

ቋንቋ ስርዓት ያለው ነው፡፡ ስርዓት አለው ስንል በቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ድምፆች በስርዓት ተቀናጅተው ቃልን፤ ቃልም በአግባቡ ከተቀናጀ በኋላ ሀረግን፤ ሀረጎችም በስርዓት እየተዋቀሩ ሰፊ የሆነውን መዋቅር ይመሰርታሉ፡፡ በስርዓት በተፈጠረው ቋንቋ አማካይነት ሰዎች እርስ በርሳቸው መግባባት ይችላሉ፡፤ ስርዓት ከሌለው ግን የሰው ልጆች በምድር ላይ እርስ በርስ ተግባብተውና ሀሳባቸውን በጋራ ተጋርተው ለመኖር ይቸገራሉ፡፡ጌታሁን(2021፣ ix) ቋንቋ ስርዓት ባይኖረው ኖሮ በቋንቋ መግባባትም ሆነ ቋንቋን ማስተማር አስቸጋሪ ይሆን ነበር፡፡ ለዚህም ነው የቋንቋን አገልግሎትም ሆነ የቋንቋን ትምህርት ከሰዋስው ነጥሎ ማሰብ የሚከብደው፡፡ አንድ ሰው በቋንቋ ሀሳቡን በትክክል ለመግለጽም ይሁን ከሌላ ሀሳብ ለመቀበል የቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም በትክክል ማወቅና አገልግሎት ላይ ማዋል አለበት፡፡ ይህ ደግሞ የአንድን የቋንቋ ሰዋስው መልመድ ወይም መማር የግድ ያደርገዋል በማለት የቋንቋውን ስርዓታዊነትና አገልግሎት ይገልጻሉ፡፡

Stem(1993፣ 131); Harmer(1987፣ 1); Brown(1994፣ 94-95) በበኩላቸው ሰዋስው የአንድ ቋንቋ የአገባብ ስርዓት የንግግር ድምፆች ምዕላድን ወይም ቃላትን ለመመስረት ከሚፈጥሩት ቅንጅት እስከ ዓረፍተነገር ምስረታ ድረስ የሚዘልቅ የአገባብ ስርዓት ነው በማለት ይገልጻሉ።

Brown(1994፣ 45) ‹‹ሰዋስው የቋንቋ ሲሆን የቃላትን የቅንጅት ስርዓት የሚመለከት በዓረፍተ ነገር ደረጃ የሚታይና የቋንቋን ተናጋሪዎች ስምምነት መነሻ ያደረገ ስርዓትን የተከተለ የቃላት አገባብ ነው›› በማለት ይገልጻሉ።

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት የምንችለው ሰዋስው በቋንቋ ውስጥ ስርዓትን የሚመለከተው ክፍል እንደሆነ ነው። የቋንቋን ስርዓታዊነት ስንል ሰዋስው ማለታችን ሲሆን፤ የቋንቋዋነኛ አገልግሎት ማግባባት ነው። የመግባባት ሂደትም እንዲከናወን ሁለትና ከዚያ የሚበልጡ ሰዎች ሊኖሩ ይገባል። ሰዎች በራሳቸው ቋንቋ ወይም በሌላ ማህበረሰብ ቋንቋ ሀሳባቸውን ለሌላው ለማጋራትና ለመግባባት የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት በሚገባ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። የሚገለገሉበትን ቋንቋ ስርዓት በአግባቡ ያልተረዱ ከሆነ ለማስተላለፍ የተፈላጊውን መልዕክት በአግባቡ ማስተላለፍ ወይም መረዳት አስቸጋሪ ይሆናል።

የቋንቋስርዓት ስለሆነው ስለ ሰዋስው ምንነት ምሁራን ከሰጡት ብያኔ አንጻር የተወሰነውን ለማየት እንሞክራለን።

> የቋንቋ ጥናት በአጠቃቀም፤ በለውጥ፤ በስርዓት ላይ ሊያተኩር ይችላል። ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርዓትን የሚመለከተው ክፍል ነው። በአሁን ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል።አ ንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ‹እውቀት› የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለው ችሎታ ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ እይታ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አዕምሯዊ እሳቤ ነው። ማለት ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ከስነ ድምፅ እስከ ስነሀረግ ያለውን ገለጻ የሚጠቁመው ነው።ይህ ፍቺ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው (ጌታሁን 2011፣ xi)።

በተጨማሪ ባየ (2004፣ ገጽ 13) ስለሰዋስው ምንነት እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ስለ ሰዋስው የነበረው ግንዛቤ በሀረግና በዐረፍተነገር አመሰራረት፤ ዓይነትና አገባብ ላይ ብቻ ስለሚያተኩር ውሱን ነበር፡፡ በድምፅ አፈጣጠርና በቃላት አመሰራረት ላይ የነበረው ትኩረት ዝቅተኛ ነበር፡፡ ከድምፅና ከቃላት በህሪ ይለቅ በፊደልና በመዝገበ ቃላት አዘገጃጀት እንዲሁም በአገባብና በትርጉም ላይ መጠነኛ ትኩረት ነበረው፡፡ በዚህም ከዘመናዊው አመለካከት ይለያል፡፡ በዘመናዊ አመለካከት የማንኛውም ቋንቋ መሰረት ድምጽ ነው፤ ፊደል የድምጽ ወኪል ነው፡፡ አወካከሉም አንድ ወጥ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ፊደል አንድን ድምጽ ብቻ ሊወክሉ ይችላሉ፡፡ ሰዋስው የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ በሀረግና በዓረፍተ ነገር ብቻ ሳይወሰን፤ የአንድን ቋንቋ ድምጽ አይነትና አቀነጃጀት እንዲሁም የቃላትን የአወቃቀር ስርዓት ይጨምራል፡፡

መሰላልነቱ ከድምጽ ጀምሮ እስከ አረፍተነገር ድረስ ላለው አጠቃላይ የቋንቋ ስርዓት ስለሆነ የአሁኑ የሰዋስው ግንዛቤ ከበፊቱ ሰፊ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ያለውን የምሁራን ሀሳብ በምናይበት ጊዜ መረዳት የምንችለው ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት እንደሆነና ከትንሹ የቋንቋ ክፍል አንስቶ እስከ ከፍተኛ መዋቅር ድረስ ስርዓቱን ጠብቆ እንዲዋቀር የሚመራና መንገዱን የሚያሳይ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ሰዋስው ከድምጽ ቅንጅት አንስቶ እስከ ዓረፍተነገር ድረስ የሚዋቀርበት ስርዓት የሚመለከት እንደሆነ ነው፡፡ ድምጽ ከድምጽ ጋር ተቀናጅቶ ቃላትን፤ ቃላት ከቃላት ጋር በተገቢው ሁኔታ ተቀናጅተው እስከ ዓረፍተ ነገር ድረስ እስካለው መዋቅር በስርዓት ካልተቀናጁ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በትክክል ላይተላለፍ ይችላል፡፡ ከድምጽ ጀምሮ እስከ ዓረፍተነገር ያለው መዋቅር በአግባቡ ከተቀናጀ የሀሳብ ፍሰቱ ሳይስተጓጎል ለማስተላለፍ የተፈለገው በማስተላለፍ ዓላማውን ሊያሳካ ይችላል፡፡

## 2.2. የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት

ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥም ሆነ በመማሪያ መጽሀፍቱ ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ የቋንቋውን ህግ ብቻ ሳይሆን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማቅረብ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ቀጥለን ስለ ሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት ከምሁራን ብያኔ ጥቂት እናያለን ፡፡

ባየ (2009፣ xxv) ከአንድ የቋንቋ ተማሪ የሚጠበቀው ችሎታ በሚመለከት ሲገልጹ ‹‹የአንድን የቋንቋ አጠቃቀም ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ አጠቃቀሙን ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ

የተሻለ ክህሎትና ስነ-ልሳናዊ እውቀት ያለው መሆኑን ያስረዳሉ››። ጌታሁን (2011፣ ix) አንድ ሰው በቋንቋ ሀሳቡን በትክክል ለመግለጽ ይሁን ከሌላ ለመቀበል የቋንቋውን ስርዓትና አጠቃቀም በትክክል ማወቅና አገልግሎት ላይ ማዋል አለበት። ይህ ደግሞ የአንድ ቋንቋ ሰዋሰው መልመድ ወይም መማር የግድ እንደሚያደርገው ይገልጻሉ። Ur (2008፣ 4-5) በበኩላቸው የሰዋሰው ትምህርት አስፈላጊነት ሲገልጹ ‹‹በአንድ ቋንቋ በአግባቡ ለመጠቀም ተጠቃሚ የሚጠብቀው ስርዓቱን ማወቅና በተግባቦት ጊዜም የሚያስፈልገውን የሰዋሰው ችሎታ መኖር ነው›› ይላሉ። በተጨማሪም Brown (1994፣ 49)። የአንድን ቋንቋ ቃላት ብቻ ማወቅ በቂ ባለመሆኑ ቃላቱ ተቀናጅተው መዋቅር የሚመሰርቱበትን መንገድ መገንዘብና እውቀቱን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ለአፈ ፊት ሆነ ለኢ-አፈፈት ቋንቋ ከተግባቦት በተጨማሪ የአጠቃቀም ስርዓቱን ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል። የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ከተግባቦታዊ አገልግሎትና ከስርዓት ጋር አቀናጅቶ ለመገንዘብ ሰዋሰውን መማርና ማስተማር አስፈላጊነት የግድ ያደርገዋል በማለት ገልጸዋል።

ከላይ ከሙሁራኑ ሀሳብ መረዳት የምንችለው የሰዋሰው ትምህርት እውቀት አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም አንድን ቋንቋ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ስርዓቱንና ህጉን መማር አስፈላጊ እንደሆነ እንገነዘባለን። ስለሆነም የቋንቋን ህግ በተገቢውና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማግኘት የሚቻለው በትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ በመማር ይሆናል። የሰዋስው ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ በመሆናቸው ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር በተመጣጣኝ ሁኔታ ተካተው ሊገኙ ይገባል።

## 2.3. በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

መማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ በውስጡ የሚያካትታቸው ይዘቶች በስርዓቱ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በስርዓት የተደራጀ የሰዋስው ትምህርት ልምድ ቀዳሚው ለተከታዩ መሰረትበሚሆን መልኩ ሊዋቀር ስለሚችል ውጤታማ ትምህርት ለማግኘት ከማገዙም በተጨማሪ ተማሪው ቀድሞ ያልተገነዘበውን እንዲገነዘብ ከመጀመሪያ ትምህርት ተከትሎ የሚመጣው ትምህርት ለማዳበር እንዲያግዘው ነው። የቋንቋ ትምህርት ልምዶች ሲደራጁ ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድ፤ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፤ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደጉ እንዲዋቀሩ ያስፈልጋል። ይዘቶችን በአግባቡ ለማደራጀት የሚቻለው

እንደየይዘቱ ስፋትና ጥልቀት የሚሄድ በአንድ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ወይም በሌላ በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት መጻህፍት ውስጥ ተደጋግሮና ተደጋግሞ ሲደራጅ ነው። Tyler (1949፣ 84) የትምህርት ይዘትን ለማደራጀት በምንነሳበት ጊዜ በትምህርቶቹ መካከል የሚኖረውን የጊዜና የቦታ ግንኙነት መመልከት እንዳለብን ይጠቁማሉ። ከዚህ አንጻር የትምህርት ይዘቶች ደረጃ በሁለት ዓይነት ሊታይ ይችላል ማለት ነው። ይህም አንደኛው በአንድ የትምህርት ዓይነት ውስጥ የሚኖረውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአንድ ደረጃ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች መካከል የሚኖረውን ዝምድና የሚያሳይ ነው። እነዚህም ግንኙነቶች ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነቶች ናቸው። ይሁን እንጂ ከዚህ ጥናት ዓላማ አንጻር በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ይዘት አደረጃጀት ከሌሎች ይዘቶች አንጻር የሚታይ ይሆናል፡፤ በተጨማሪም በተመሳሳይ ይዘት በራሱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተዋረዳዊ አደረጃጀት ከሳምንት አንድ እስከ መጨረሻ የትምህርቱ ሳምንት ያለው የሚታይ ይሆናል። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አደረጃጀቶች ለማየት እንሞክራለን።

### 2.3.1. ተከታታይነት

የትምህርት ይዘቶች ተዋረዳዊ ግንኙነቶችን የሚያመለክተው ተከታታይነት ነው። አደረጃጀቱም በአንድ የትምህርት ዓይነት ይዘቶች ውስጥ የሚኖረውን መደጋገም የሚያሳይ ነው። በአንድ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በሚቀጥለው ይዘቶችና ምዕራፎች እየተከታተለ መምጣቱን የሚያመላክት እንደሆነ ገልጸዋል። ከላይ ከምሁሩ ሀሳብ መረዳት እንደምንችለው የትምህርት ይዘት በሚደራጅበት ጊዜ የአንዱ ሳምንት ከቀጣዩ ሳምንት የትምህርት ይዘት ጋር እየተደጋገመ መኖሩን ወይም መገኘቱን የሚያሳይ ነው። ትምህርት ረዥም ጊዜና የማያቋርጥ ክትትል የሚያሳይ ጉዳይ እንደመሆኑ በውስን የትምህርት ይዘት የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ግቡን ይመታል ተብሎ ስለማይታሰብ ተደጋጋፊነት ያላቸው የትምህርት ልምዶች እየተደጋገሙ ደረጃ በደረጃ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

### 2.3.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት ለማስተማሪያ የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና በተከታታይ ባሉ ክፍሎች ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። ቀለል ካለው በመጀመር እያደገ ወይም ከፍ እያለ የሚሄድ መሆን

ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ ክፍሎች ተመሳሳይ ይዘት በተመሳሳይ የቅለት ደረጃ የሚዘጋጅ ከሆነ ተማሪዎቹ ላይ የመሰላቸት ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህ እንዳይሆን ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደገ የሚሄድ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተለጣጣቂነት በማስመልከት ተስፋዬ ሸዋዬ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> በአንድ የማስተማሪያ መሳሪያ ውስጥ ባሉ ልዩልዩ ምዕራፎች መካከልና በተለያዩ ክፍሎች የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ተለጣጣቂነት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ በመሰረቱ ተማሪው የሚያደርገው የመማር ጥረት በየጊዜው እያደገ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡ ቀጥሎ የሚደርስበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ፤ ቀጥሎ የሚነበበውም መጽሀፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት፡፡ ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን ዕድገት ወይም አዲስነት የለበትም መሰላቸት ይከተላል (ተስፋዬ፣ 1981፣ ገጽ 94-95)፡፡

ከላይ ከምሁሩ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ የማስተማሪያ ውስጥ እና በተለያዩ ክፍሎች የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ተለጣጣቂነት መኖሩ የግድ እንደሆነ በመግለጽ፤ ተማሪውም የሚያደርገው የመማር ጥረት በየጊዜው እያደገ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ እንዳለበትና አሁን ያለበት ቀጥሎ ከሚማረው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል እንዳለበትና ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን ዕድገት ወይም አዲስነት እንደሌለበት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ጥናትም ከዓላማው አንጻር ከሌላ ክፍል ጋር ያለው የሚታይ ሳይሆን በተተኳሪው ክፍል ውስጥ ያለውን የይዘቶች ሁኔታ ከመጀመሪያው ሳምንት እስከ መጨረሻው ሳምንት የሚታዩ ይሆናል፡፡

### 2.3.3. መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት

መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት በተመለከተ Cunningsworth (1984) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ አንድ ይዘት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሲደራጅ ተማሪዎች ደረጃ በደረጃ እየተማሩት ስለጉዳዩ የሚኖራቸውን ግንዛቤ እያሳደጉ እንዲሄዱ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለምሳሌ የሰዋስው ይዘትን ብንወስድ ከቃል ምስረታ ወደ ሀረግ ምስረታ ከዚያም ወደ ዐረፍተ ነገር ምስረታ እያለ የሚያሳየውን መስመራዊ የሽግግር እድገት እና ያመጣውን ለውጥ እንዲሁም ሂደቱን ጠብቆ የሚሄድ ሁኔታ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

### *2.3.4.* ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ተማሪዎች ከቋንቋ ዝርዝር ሁኔታ ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው የቋንቋ ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ Cunningsworth (1995፣ 78) እና Woods (1995፣ 76) “”ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መነሻ አድርገው የተሰጣቸውን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋውን ህግ እራሳቸው እንዲደርሱበት የሚያደርግ ነው›› በማለት ገልፀዋል፡፡

ከላይ ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ተማሪዎቹ የቀረቡትን ምሳሌዎች መነሻ አድርገው የተሰጣቸውን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋውን ህግ እራሳቸው እንዲደርሱበት የሚያደርግ ስልት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

### 2.3.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

ከዚህ አደረጃጀት የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚካተቱት የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ፣ መዋቅርና ሌሎች ህግጋትን ለተማሪዎች በቀጥታ ለማስተማር ታስቦ ሲሆን ዋናው ዓላማውም ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ከተማሩ ለሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢ ነው ብለው ባመኑበት በቋንቋው መጠቀም ይችላሉ (Grant 1989፣ 12)፡፡ በተጨማሪም Cunningsworth (1995፣ 99) ‹‹ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት የቋንቋውን ዋናዋና ህግጋት፣ ገለጻዎችና ምሳሌዎች ለተማሪው እየቀረበለት እንዲያውቅ ከተደረገ በኋላ ዝርዝር መልመጃዎችን በመስጠት ትክክለኛውን የቋንቋ እውቀት እንዲረዳ የሚደረግበት ስልት ነው›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ትኩረት የሚያደርገው የቋንቋው መዋቅሮችና ህግጋትን ለተማሪዎች አስቀድሞ በማቅረብ እንዲያውቁ ከተደረገ በኋላ ዝርዝር መልመጃዎችን በመስጠት ትክክለኛውን የሰዋስው የቋንቋ ዕውቀት እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

## 2.4. በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

Bygate and et al, (1994፣ 45-53) እንደገለጹት ‹‹የቋንቋ ህግጋት (የሰዋስው ክፍሎች) ለመማር ማስተማር ዓላማ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሲደራጁ ግልፅነት፣ ትክክለኛነት፣ ተመጣጣኝነትና ተገቢነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል›› ይላሉ። እያንዳንዳቸውን ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

### 2.4.1. ግልፅነት

አንድ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መጽሀፍ ውሰጥ ሲደራጅ ለተማሪው ግልፅ በሆነና ሊረዳው በሚችል መልኩ መሆን አለበት። አንድ የትምህርት ይዘት ጥሩ አቀራረብ አለው የሚባለው ግልጽ ሆኖ ሲቀርብ ነው። ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንጻርም ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በመረዳት ረገድ ምንም ችግር እንዳይገጥማቸው ማለትም የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ተማሪዎቹ ሊረዱት የሚችሉት መሆን አለበት። ይህንንም ለማድረግ የቀረቡ ገለጻዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና መልመጃዎች ግልጽና የማያሻሙ፣ የማያጠራጥሩ እንዲሆኑ ይመከራል። ይህም ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ ተካተው የቀረቡላቸውን የሰዋስው ትመምህርት ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን ለመረዳት እንዲሁም መልመጃዎችን ለመስራት በሚሞክሩበት ወቅት በራሳቸው ከግልጽነት አንጻር የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያቃልልላቸው ይችላል (Harmer፣ 1987)::

> ተስፋዬ (1981፣ ገጽ 94) በበኩላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች የያዙአቸው የትምህርት ጉዳዮች መምህር እንዲያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልጽ መስፈርት አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው። ግንዛቤ እንዲገኝባቸው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ጉዳዮች ምንነታቸው በማያሻማ ስልት እንዲቀርብ ያስፈልጋል። እንዲያውም በማስተማሪያዎቹ አማካይነት ለትምህርት የቀረበው ጉዳይ ምንነትና የትምህርቱ ዓላማ ጥምር ግልጽነት እንዲኖራቸው ይጠበቃል በማለት ገልፀዋል።

### 2.4.2. ትክክለኛነት

Swan (1994) እንደሚያስረዱት ትክክለኛነት ዕውነተኛ የቋንቋውን ስነልቦናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ይዘት ይመለከታል። ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ትክክልና እውነተኛ ሊሆን ይገባል። በእርግጥ የታላሚውን ቋንቋ አንዳንድ ሰዋስዋዊ

ክፍሎች ትክክለኛ ቅርጽ ማሳየቱ ለተማሪዎች ዕድሜና የትምህርት ደረጃ አንጻር ከባድና ውስብስብ ሊሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም በተቻለ መጠን ተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ለተማሪዎች ትክክለኛውን የቋንቋ ስርዓት ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

ተስፋዬ (1981፣ ገጽ 94) እውነተኛነት ሲባል ያ ለትምህርት የቀረበው የቋንቋ አካል ወይም ክፍል ዕውነት የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚለው መሆን አለመሆኑ የሚዳኝበት ነው፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ለተወሰነ ደረጃ የሚመጥን ወይም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የሚመጣ የቋንቋ ክፍልን ህብረተሰቡ የቋንቋው ባለቤት እንዲገለገልበት አድርገው ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ተማሪው እንዲማር የሚቀርብለት እንዲለምደው የሚያደርገው የቋንቋ አካል ወይም ክፍል ቋንቋውን ይበልጥ የሚያሰውቅ፤ በቋንቋው ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድር መሆን አለበት በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከገለጻዎቹ በመነሳት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ ሲሞከር ተማሪዎቹ ውስጥ የጥርጣሬ መንፈስ ሳይኖር ትክክለኛውን ለተማሪዎች ለማቅረብ ጥረት ማድረግ እንዳለብን ያስረዳል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ለማስተማር በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች ትክክለኛውን የሰዋስው ትምህርት ባህሪ  ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ይዘቶች በአግባቡ ትክክለኛና በእውነት ላይ የተመሰረተ ነገር ተከትለው ለተማሪው በማያወዛግብና በማያጠራጥር ሁኔታ መዘጋጀት አለበት፡፡

### 2.4.3. ተገቢነት

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ይዘቶችከተማሪዎች ዕድሜ፤ የቋንቋ ችሎታ፤ የግንዛቤ ደረጃ፤ ዳራና የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ታይቶ ሊመረጥ ያስፈልጋል፡፡ (Sheldon፣ 1988) ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፤ ችሎታ፤ የግንዛቤ ደረጃ ጋር የተጣጣሙ በመሆናቸው ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው ይችላሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

Harmer (1987፣ 19) በተጨማሪም ‹‹የአንድ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ የቋንቋ ቅርጾች፤ ፍችና አጠቃቀም ሁኔታ አንጻር ለማስተማር የሚያስችሉና ተገቢነት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል›› በማለት ያስረዳሉ:: ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንገነዘበው በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች ዕድሜ፤ የትምህርት ደረጃ እንዲሁም ማህበራዊ

ሁኔታ የተጣጣሙ መሆን አለባቸው ካልሆነ ግን ተማሪዎቹ በቀላሉ መረዳት ስለማይችሉ አስቸጋሪ እንደሚሆን ነው። ስለዚህ የሚዘጋጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

### 2.4.4. ተመጣጣኝነት

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ከቋንቋው ክሂል ዘርፎች ማዳመጥ፤ መናገር፤ ማንበብ፤ መጻፍ ሰዋስውና ስነፅሁፍ ይዘቶች ውስጥ ተመጣጥነው የተውጣጡ መሆን ይኖርባቸዋል። የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከስነድምፅ እስከ ስነፍቺ ድረስ ያሉትን የሚያመላክቱ ሲሆን ሁሉም በተመጣጠነ መልኩ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፤

Harmer(1987፣ 18) የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲደራጁ ከቋንቋው ክሂል ዘርፎች ከሰዋስውና ከስነጽሁፍ ይዘቶች ጋር ተመጣጥነው መቅረብ አለባቸው፡፤ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፍ ውሰጥ የሚኖራቸው ስርጭት ከታላሚው ቋንቋ ልዩልዩ ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። የሰዋስው ይዘቶችም ከቋንቋ ድምጽ ስርዓት፤ ምዕላድ፤ ስነአግባብና ስነፍች የተውጣጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፤

በተጨማሪም Larson Freeman (1991፣ 280); እና Cunningsworth በተመሳሳይ ሁኔታ ‹‹በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ቋንቋውን ስርዓት ባለው መንገድ ተገንዝበው በትክክለኛው መንገድ እንዲገለገሉ ማስቻል አለበት››። ይህንን ከግብ ለማድረስ እንዲቻል የሰዋስው ይዘቶች ከሁሉም ክፍሎች የተውጣጡ ሆነው መካተት ይኖርባቸዋል።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው በመማሪያ መጽገሀፍ ውስጥ የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶች በዓይነትም ሆነ በመጠን ተመጣጥነው መቅረብ አለባቸው። ለተወሰኑ ይዘቶች ብቻ ትኩረት የሚሰጥ የአቀራረብ ሁኔታ አስፈላጊ አለመሆኑን ነው። ማለትም ለአንድ የትምህርት ይዘት ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ሌላውን መዘንጋት አይገባም በተቻለ መጠን ሁሉም ይዘቶች ተመጣጥነው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

ስለመርሀ ትምህርት፤ስለመማሪያ መጻህፍት፤ እንዲሁም ስለ ሰዋስው ምንነትና አስፈላጊነት ይህን ያህል ካነሳሁ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ስላላቸው ቀደምት ጥናቶች ለማየት እንሞክራለን።

## 2.5. የቋንቋ መርሃ ትምህርት ምንነት

የቋንቋ መርሃ ትምህርት ምንነት ስርዓተ ትምህርቱ የሚነሳና ጠበብ ባለ መልኩ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት ምን መማር እንዳለባቸው የሚያመላክት ሰነድ ሲሆን በውስጡም የትምህርቱን ዓላማ ግብ መምታቱ፤ ይዘትና የይዘቱን አቀራረብ፤ የትምህርቱን ጊዜና ዓላማው የሚፈተሸበትን ግምገማ የያዘ ሰነድ ነው (Cunningsworth 1995 እና Dubin and Olshtain 1986፣ 35)።

Cunningsworth (1989፣ 22), Hutchinson and Waters (1989፣ 65), Ur (1996፣ 176) ጠቅሰው እንደገለፁት መርሀ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት በበለጠ መልኩ የአንድ የትምህርት ዓይነቶችን ለማዋቀር በመነሻነት የሚያግዝ፤ የትምህርት አጣቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን በመግለጽ የሚያሳይ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም ትምህርቱ የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ የሚያመላክት የምዘና ስልቶችንና መረጃ መሰሪያዎችን የሚጠቁም ንድፍ ወይም ሰነድ ነው።

በመሆኑም መርሀ ትምህርት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት በየክፍል ደረጃው የሚዘጋጅ ሰነድ ሲሆን ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላ የክፍል ደረጃ የሚያደርሰውን አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ዋን ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎችን፤ የትምህርት ይዘቶችን፤ መርጃ መሰሪያዎችን፤ የመምህሩንና የተማሪውን ተግባር፤ የማስተማሪያ ዘዴውን፤ ከተማሪዎች ችሎታ፤ ፍላጎት፤ ዕድሜ፤ የብስለት ደረጃ ፤ ዳራዊ ዕውቀት ጋር አገናዝቦ በጊዜ ገደብ ሸንሽኖ ለማቅረብ ይረዳል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Cari Wenning (2009፣ 1-2) መርሀ ትምህርት የአንድ ሀገር የትምህርት ስርዓት መነሻ አድርጎ የሚዘጋጅና ተማሪዎች በምን ዓይነት ሂደት ምንና እንዴት ማወቅ እንዳለባቸው፤ መምህራንም እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው፤ የሚጠቁሙ መሰረታዊ የሆነ የትምህርት ስራ ዋና አካል እንደሆነ ይገልፃሉ።

መርሀትምህርት የአንድ ተተኳሪ ትምህርት የክፍል ደረጃ ያገናዘበ መሪ ዕቅድ ወይም ዝርዝር ዕቅድ ነው። ይህ ዕቅድ የሚከተሉት አምስት መሰረታዊ ነጥቦችን የሚገልጽ ሰነድ መሆኑን ዓለም (1997፣ገጽ 178-179) Hutchinson and Waters (1991)ን ጠቅሰው ይገልጻሉ። እነሱም በመርሀ ትምህርቱ

የተነደፈው የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ሲጠቃለል ተማሪዎች ምን እንዲያውቁ ይጠበቃል? ዓላማዎችን የሚመለከት ሲሆን ዓላማዎቹ ደግሞ መሰረትን የጠበቁና ግብ መቺ ሆኖ መቅረብ አለባቸው፤ ተማሪዎቹ ንዲማሩ የሚያደርገው ጉዳይ ምንድን ነው? ይዘቶችን የሚመለከት ሲሆን ይዘቶች ተብራርተው መቅረብ አለባቸው፤ ተማሪዎች ትምህርቱን የሚማሩት ለምን ያህል ጊዜ ነው።/የክፍለ ጊዜ ርዝማኔን ይመለከታል። ተማሪዎች ትምህርቱን የሚማሩት እንዴት ነው? የማስተማሪያ ስልቶችንና የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምን ይመለከታል። ተማሪዎች ከድህረ ትምህርት በኋላ እንዴትይመዘናሉ? /ግምገማን ይመለከታል።/ የሚሉትን ጥያቄዎች በማብራራት ፍንጭ የሚሰጥ ሰነድ ነው።

## 2.6. የመርሀ ትምህርት ዓላማ

የመርሀ ትምህርት ዓላማዎችን አስመልክቶ Hutchinson, and waters (1987) እንደሚከተለው ይገልጹታል። መርሀ ትምህርት የቋንቋ ትምህርትን በመጽሐፉ ውስጥ በምእራፍ መጥኖ ለማቅረብና ለማስተማር በሚያስችል መልኩ ለማቅረብ ይረዳል። ይህም ለመምህራንና ተማሪዎች የሞራል እገዛ ያደርጋል። ለተማሪዎችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ትምህርቱ በአግባቡ የተዘጋጀና የታቀደ መሆኑን ያረጋግጣል። ለተማሪዎችና መምህራኑ ትምህርቱ ከየት ወዴት እንደሚሄድ አቅጣጫ ያሳያል፤ የትምህርቱ አዘጋጆች የቋንቋ መማርን በተመለከተ ምን ዓይነት እይታ እንዳላቸው ለማየት ያስችላል። እንዲሁም ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚማሩም ጭምር ይናገራል። በማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ ምንባቦችና መልመጃዎች መረጣን በተመለከተ መመሪያ ይሰጣል። በትምህርት ስርዓቱም ሆነ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ወጥ በሆነ መልኩ ትምህርቱ እንዲሰጥ ያደርጋል። ተማሪዎች በትምህርት አሰጣጡ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ሙከራ በመስጠት ለመመዘን መሰረት ይሆናል በማለት ያብራራሉ።

## 2.7. የመርሀ ትምህርት ጠቀሜታ

መርሀ ትምህርት በእቅድ ለመመራት ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ነው። መርሀ ትምህርት የሚሰጠውን ትምህርት ዋና ዓላማና እንዲሁም ዝርዝር ዓላማዎችን የያዘ ከመሆኑም ባሻገር ለትምህርቱ ወሰን /ገደብ/ ለማበጀት ይረዳል። የአገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍልስፍና መሰረት

በማድረግ ይዋቀራል፡፡ ከተማሪዎቹ አቅምና ፍላጎት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንበ ማጣጣም ትምህርቱን ለመስጠት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የመርጃ መሳሪያዎች መርጦ ለመጠቀም ከመርዳቱም በላይ የማስተማሪያ ናሙናዎችን ይጠቁማል፡፡

## 2.8. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ሆን ተብለው የሚዘጋጁ ሲሆኑ፤ በእያንዳንዱ ተማሪ እጅ መገኘት ያለባቸው ሆነው መልመጃዎችንና ደረጃቸውን የጠበቁ ምንባቦችን የያዙ ሰነዶች ናቸው፡፡ መማሪያ መጻህፍቱ ሲዘጋጁ የታላሚውን ቋንቋ የፀደቀውን መርሀ ትምህርት መነሻ ተደርጎ ነው፡፡ መማሪያ መጻህፍቱ ሲዘጋጁ የታላሚውን ቋንቋ ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ ይዘቶችን በማካተትና የመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማ ለማድረግ ታቅዶ የሚዘጋጁ ሰነዶች ናቸው፡፡ እንዲሁም በመምህሩና በተማሪው መካከል ያለውን የመማር ማስተማር መስተጋብር ለማቃናት አስቀድሞ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ስለ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ምሁራን ካነሱት ሀሳብ የተወሰነውን ለማየት እንሞክራለን፡፡

ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት የታላሚውን ቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋውን ስነልሳናዊና ስነ ትምህርታዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስነ ልሳናዊ ይዘቶች ስንል በታላሚው ቋንቋላይ ያሉትን ድምፆች፣ ቃላት፣ ዓረፍተ ነገሮች ወዘተ… ይመለከታል፡፡

ይህም አንድ ድምጽ ከሌላ ድምጽ ጋር ሲቀናጅ ምን ዓይነት ባህሪ እንደሚያሳይ፤ አንድ ቃል በዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን አግባብና አገልግሎት ምን እንደሚመስልና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች አንዱ ለሌላኛው መሰረት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ኢ-አፈፈት ተማሪዎች ድምፆችን ሳናስተምር ቃላትን ማስተማር አንችልም፤ እንዲሁም ቃላትን ሳናስተምር ዐረፍተ ነገርን ማስተማር አንችልም፡፡ ስለዚህ ስነ ልሳናዊ ይዘት ከምን ተነስተን ምን እንደምናስተምርና ምን ላይ ማተኮር እንዳለብን ለመወሰን ይረዳናል፡፡ ስነ ትምህርታዊ ይዘት ስንል ደግሞ ተማሪው ቀድሞ ምን ተምሯል? ምን ዓይነት ይዘት ይፈልጋል? በቋንቋ ምን መጠቀም ይፈልጋል? ይዘቶቹ እንዴት መቅረብ አለባቸው?

እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል። ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ ስነ ልቦናዊና ስነ ትምህርታዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው በማለት Dubin and Olishtain (1992፣ 45) ላይ ይገልጻሉ።

በተጨማሪም Grant (1987፣ 5) እና Shelden (1987፣ 1) መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ የትምህርት ዓላማዎችን የያዘ፣ ለዓላማ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ተመጣጣኝ፣ ተለጣጣቂና ተደጋጋፊ ይዘቶችን በውስጡ አደራጅቶ የያዘ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ለማስተማር የሚያገለግል መሳሪያ ነው። መማሪያ መጽሀፍ አንዱና ዋና የትምህርት መሳሪያ በመሆኑ ከብዙ ነገሮች አንጻር ተገምግሞ በጥንቃቄ መዘጋጀት አለበት። ምክንያቱም በመርሀ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ በግልጽና በዝርዝር ያልሰፈሩ ይዘቶች የሚቀርቡ በመሆናቸው ነው። የመርሀ ትምህረቱም ሆነ የመማሪያ መጽሀፉ ተቀዳሚ ዓላማ የተማሪውን የስነ ልሳንና የቋንቋ ተግባቦትን ለማዳበር እንዲረዱ ተደርገው ለማስተማሪያ የሚዘጋጁ መሳሪያዎች እንደሆኑ ይገልጻሉ።

## 2.9. የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት ግንኙነት

መርሀ ትምህርት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያ የስርዓተ ትምህርት አካል መሆኑ ተገጧል። ተግባራዊነቱ የሚተገበረው ደግሞ በመማሪያ መጻህፍት አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሀፉ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ሁኔታ ለትምህርቱ ውጤት መሳካት የራሱ የሆነ ገንቢ ሚና ይኖረዋል። በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሀፍ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ተዛምዶ የተለያዩ ምሁራን ሀሳብ ሰንዝረዋል Grant (1987)። የመማሪያ መጽሀፍ ከመርሀ ትምህርት ጋር የቅርብ ተዛምዶ ሊኖረው እንደሚገባና ተዛምዶ ከሌለው ግን ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል ገልጸዋል።

Richardsand Rodgers (1986፣ 25-26) እና Shelden (1987፣ 78) በመስኩ ባለሙያዎች ተገቢ የሆነ ጥናታቄና ትኩረት ተሰጥቶት የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጫወቱት ሚና ከፍ ያለ መሆኑን ይገልጻሉ። የማህበረሰቡን የዕድገት ደረጃ ወግና ባህላቸውን እንዲሁም እምነትና ፍላጎታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለተማሪው፤ ለመምህሩና ለአጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት እጅግ አስፈላጊ ናቸው በማለት ይገልጻሉ።

ከዚህ በላይ ከምሁሩ ሀሳብ እንደተረዳነው የቋንቋ መማሪያ መጻሀፍት እጅግ አስፈላጊና ጠቀሜታ ያላቸው እንዲሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም መምህሩንና ተማሪውን በማስተሳሰር የትምህርት ስርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል፡፡ መማሪያ መጻህፍቱ መምህሩንና ተማሪውን በማገዝ አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ መማሪያ መጽሀፍት ከላይ ያየናቸውን አገልግሎቶች የሚሰጡ ከመሆናቸው አንጻር እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ሁሉም ነገር ተስተካክሎን አሟልቶ ይይዛል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በውስጡ ያሉትን በመፈተሽ ጠንካራ ጎኑ መበረታታት ያለበት ሲሆን ደካማ ጎኑ ደግሞ መደገፍና መሻሻል ይኖርበታል፡፡

## 2.10. የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነትና ተቀራራቢነት ያላቸውንተዛማጅ ጥናታዊጽሁፎች እንደሚከተለው ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ሲሳይ ቴሌ (2007 ዓ.ም.)ለድህረ ምረቃ ማሟያ የቀረበ ጥናት ትኩረቱ ከ2001- 2006 ዓ.ም. በተሰጡት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና አቀራረብ ግምገማ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የሰዋስው ይዘት ትምህርት ይዘትን በሚመለከት ብቻ ሲሆን ዓላማውም የተለያየ ነው፡፡ ጥናቱ የተሰራውም በ10ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ ስለሆነ የክፍል ደረጃውም ግንኙነት የለውም፡፡ ተቀራራቢነት ያላቸው የሰዋስው ይዘቶችን ከፈተና ውስጥ የሚመለከት በመሆኑ ብቻ የሰዋስው ይዘት የሚለው ስለሚያገናኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአጥኚው ትኩረት የሰዋስውን አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር የሚቃኝ በመሆኑ ተቀራራቢነት እንጂ ተመሳሳይነተ የላቸውም፡፡ የአጥኚው ትኩረት ፈተና በመሆኑ መማሪያ መጽሀፍ የማይፈትሽ ስለሆነ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሰሚራ (2010 ዓ.ም.)በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም.ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በሚል ርዕስ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡የጥናቱ ትኩረት የሆነው የትምህርት ክፍል የ8ኛ ክፍል ሲሆን የታተመውም በ2009 ዓ.ም. ነው፡፡ ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳዩ አንጻር ተመሳሳይነት ያለው ይመስላል፡፡ ይኸውም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መፈተሽ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ቢመሳሰልም የክፍል ደረጃው ግን ልዩነት ያለው በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሌላው አስቴር (በ2011 ዓ.ም.)የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ በ2004 ዓ.ም. ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስወ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መፈተሽበሚል ርዕስ የተሰራ ነው። የአጥኚዋ ተተኳሪ ክፍልና ዓመተ ምህረት ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት የለውም። በአንጻሩ ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት በሚለው ተመሳሳይነት አለው። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሀሳብ ያለው ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ግን ልዩነት አለው።

በተጨማሪም በባዩ (2005 ዓ. ም.) በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን አማርኛ መማሪያመጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት በሚል ርዕስ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ ትኩረት የሆኑት የትምህርት ክፍሎች ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ናቸው። እነዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በተለያዩ ዘመን የታተሙ ሲሆኑ 5ኛ እና 6ኛ ክፍሎች በ1998 ዓ.ም. የታተሙ ናቸው። የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ደግሞ በ1997 ዓ.ም. ታትመዋል። ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳዩ አንጻር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ይኸውም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መፈተሽ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት ቢኖረውም የክፍል ደረጃውና የታተመበት ዘመን ግን ልዩነት ያለው በመሆኑየተለየ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸውን ከእኔ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሁፎች ሲሆን አጥኚዎቹም በተለያየ ጊዜ፤ የክፍል ደረጃና በተለያየ ዓላማ ሆኖ የሰዋስው ይዘትን በሚመለከት የሰሩት ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። ጥናታዊ ጽሁፎቹም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በተወሰነ መልኩ የሰዋስው ይዘትን በሚመለከት ግንኙነት ያላቸው ቢሆኑም ሙሉ በሙሉ ከእኔ ጥናት ጋር ግን ተመሳሳይ ካለመሆናቸውም የተነሳ ተቀራራቢ ጥናቶች መሆናቸውን ለማየት ተችሏል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዓይነታዊ ምርምር ተግባራዊ ይሆናል። ዓይነታዊ ምርምር ስለሚያጠናው ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት በመመርመርና በመፈተሽ ያለውን ሁኔታ ያስቀምጣል ያለው (2009፣ ገጽ 19)። ስለዚህ የተተኳሪው ጥናት መነሻ በሶስተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ይመስላል የሚለውን መፈተሽ ስለሆነ በዚህ ዘዴ በመጠቀም አጠቃላይ አደረጃጀቱን፤ አቀራረቡን፤ እንዲሁም የሚታዩትን ድክመትና ጥንካሬ በስፋትና በጥልቀት የሚያሳይ ይሆናል። በመሆኑም ለዚህ ጥናት በደንብ ለመተንተንና ለመግለጽ በዋናነት ዓይነታዊ ምርምር በተግባር ላይ ይውላል።

ጥናቱም በአቀራረቡ ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎችን በአብዛኛው በማብራራትና በመግለጽ የሚያቀርብ ይሆናል። ያለው (2009፣ ገጽ 20) ላይ ‹‹ገላጭ ምርምር በጥናት የተተኮረው ችግር ምን እንደሚመስል የሚያሳይ፤ ስለ ችግሩ ስፋት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የሚገልጽ፤ የችግሩን መልክ ለመለየትና የምርምሩን አቅጣጫ ለመወሰን የሚያስችል ነው።›› በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ለመስጠት ገላጭ ምርምር ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል።

### 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓይነት መሰረት በማድረግ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠቀም ይቻላል። በመሆኑም ለዚህ ጥናትለመረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግል ሆኖ የታሰበው የሰነድ ፍተሻ ነው። በዚህ መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ በሆነው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና ለደረጃው በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ የተካተቱትን የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ለመመርመር የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ በመሆን አገልግሏል።

ለዚህ ጥናት ሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ እንዲሆን የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት የጥናቱ አብይ ትኩረት የሆነው በ2009 ዓ.ም. የታተመው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

መማሪያ መጽሐፍእና ለዚሁ የክፍል ደረጃ የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት መገምገም ስለሆነ ከተተኳሪው አንጻር ሰነድ ፍተሻ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ስለዚህ ግምገማው በሚካሄድበት ወቅት በክለሳ ድርሳናት በሚቀርበው ሀሳብ መሰረት በማድረግ አደረጃጀቱና አቀራረቡ የሚታይና የሚተነተን በመሆኑ የተሻለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሰነድ ፍተሻ ሆኖ ተገኝቷል።

## 3.3. የመረጃ ምንጭ

በዚህ ጥናት ውስጥ በዋናነት የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው በ2009 ዓ.ም. ታትሞ ስራ ላይ የዋለው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሲሆን፣በተጨማሪም ለዚሁ ክፍል ደረጃ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል። በእነዚህ ሁለት ምንጮች ውስጥ ያሉት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ትኩረት ተደርጎባቸዋል።

## 3.4. የናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ትኩረት በ2009 ዓ.ም.የታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት መፈተሸ ሲሆን ለዚህ ጥናት ያመች ዘንድ የተመረጠው ወሰኝ ናሙና ዘዴ ነው። ወሰኝ ናሙና በውስጡየተለያዩ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎችን ያካተተ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ በጥናቱላይ መነሻ በማድረግ የዓላማ ተኮር ናሙናንአገልግሎት ላይ እንዲውል ተመርጧል።ያለው (2009፣ ገጽ 136) ስለ ዓላማ ተኮር ናሙና “በዚህ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ነው። እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡን ይችላሉ? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝበት እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ይመርጣል።“ በማለት ይገልጻሉ።

ስለሆነም የዚህ ጥናት የናሙና ዓይነት ዓላማ ተኮር ናሙና እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት ከጥናቱ ዓላማ አንጻር የተሻለ መረጃ ይገኝበታል ተብሎ ስለታሰበ ነው።

## 3.5. የመረጃ አተናተን

ይህ ጥናት መሰረት የሚያደርገው ዓይነታዊ ምርምርን ነው። የጥናቱ ትኩረትም በ2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀትን መገምገም ነው። የዚህ ጥናትየመረጃ አተናተን በተመለከተ ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ሲሆንይኸውም ጥናቱበዋናነት ለደረጃውየተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፍ መነሻ ተደርጎ የቀረበውን የተተኳሪው ክፍል መርሃ ትምህርትን መፈተሽ ተችሏል። በመቀጠልም ሰነዱ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በየደረጃው በመለየት ከስነ ድምጽ ጀምሮ ስነ ምዕላድ፣ ስነ ሀረግ፣ ስነ አገባብና ስነ ፍች በማለት በየዓይነታቸው ማስቀመጥ ሲሆን ከነዚህም ተለይተው የተቀመጡትን የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀታቸው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ባለው ትኩረት አንፃር መደራጀታቸውን መፈተሽ ተችሏል። በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ይዘት መልመጃዎች በመልመጃ ማደራጃ መርሆች አንጻር መደራጀታቸውን በመፈተሽ ትንተናው ተካሂዷል። እንዲሁም የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች በየምዕራፉ ካሉት የሰዋስው ይዘቶች ጋር ተዋረዳዊ ግንኙነት አላቸው ወይ የሚለውን በመፈተሽ ለማሳየት ተችሏል። ትንተናው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተገኘውን መረጃ ዓይነታዊ ምርምር ዘዴ አካል በሆነው ገለፃዊ ዘዴ መሰረት በማድረግ ተተንትኗል። ከመጽሐፉ ውስጥ ከሰዋስው ትምህርት ይዘት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መልመጃዎችን የተወሰኑትን ለአብነት በመውሰድ በገለፃ እንዲብራራ ተደርጓል። በተጨማሪም በሰንጠረዥ መልክ ቀርቧል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ዓላማ ከግብ እንዲደርስ በመጀመሪያ የጥናቱ ትኩረት የሆነውን መጽሐፍ ደጋግሞ በማንበብና በመፈተሽ እና መረጃ በማሰባሰብ በየአይነታቸው በመለየት ማስቀመጥ ቀዳሚው ሲሆን በመቀጠልም አስፈላጊ ያልሆኑትን መረጃዎች በመለየትና በማውጣት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት በማየት መተንተንና መግለጽ ተችሏል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ የሆነው በ2009 ዓ.ም. ታትሞ በስራ ላይ የዋለው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋየተማሪ መፅሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳን ውስጥ በተገለጹት የአደረጃጀትና አቀራረብ መርሆዎች መሰረት ይተነተናሉ። ተተኳሪው የመማሪያ መጽሐፍ ለደረጃው በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ በተሰጠው ትኩረት አንፃር እየተፈተሸ ይተነተናል። በቅድሚያ ግን ስለተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውጫዊና ውስጣዊ ገጽታ አጠር ያለ ቅኝት ይቀርባል።

### 4.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ገጽታ (ቅኝት)

የሶስተኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ፌደራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በ2009 ዓ.ም. የተዘጋጀ አንደኛ ዕትም። የታተመው በአሜሪካ አለም አቀፍ ድርጅት (USAID) ትብብር በህንድ ሀገር (ፒታምብራ) መጽሐፍ ማተሚያ ድርጅት ነው። ከመጽሐፉ ውጫዊ ገጽታው ስንነሳ የሽፋን ቀለሙ ቀይ ሆኖ ከግርጌው ሮዝ መልክ ያለው ሲሆን በመጽሐፉ ሽፋን የፊት ለፊት ገጽ ላይ ከራስጌ በኩል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት እና የደቡብ ክልል ባንዲራ ስዕል ተስሏል። ከባንዲራው ቀጥሎ “አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ” የሚል ጽሑፍ ተጽፏል። መሀል ላይ የአራቱም ቋንቋ ኪሂሎች ማለትም የመናገር፤ የማዳመጥ፤ የመጻፍና የማንበብ ኪሂሎችን የሚያመለክቱ፤ ቁልፍ እና የተጨባበጡ እጆች ስዕሎች ተስለዋል።

የመጽሐፉ የስረኛው ግርጌ ላይ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የሚል ጽሑፍና አርማ በቀኝ በኩል ፤ በፊት ለፊት በጀርባ ሽፋን ላይ ይገኛል። በተጨማሪም በጀርባ ሽፋን ላይ “አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 3ኛ ክፍል” የሚልና ከስር በስተግራ በኩል የመጽሐፉ ዋጋ -- የኢትዮጵያ ብር ሃያ መሆኑ ተገልጧል።

ከመጽሐፉ ውጫዊ ሽፋን ወደ ውስጣዊ ገጽ ስንገባ በሽፋኑ በውስጠኛው በኩል ተማሪዎቹ መጽሐፉ እንዳይበላሽ ማድረግ ያለባቸውን አስር የጥንቃቄ መመሪዎች ተጽፈው እናገኛለን። ከሽፋን ገጽ ቀጥሎ ባለው የውስጠኛው የመጀመሪያ ገጽ ላይ በስተግራ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ባንዲራ እና በስተቀኝ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ባንዲራ ተስሎ ይገኛል። ከባንዲራዎቹ ስር አማርኛ በትላልቁ መጠንና እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 3ኛ ክፍል የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል። በመቀጠልም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሚክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት

ሚኒስቴር የተጻፈ ሲሆን አስማምቶ አዘጋጆች እና የጥራት ክትትል ስም የሚጠቁም መረጃ አለ። በስተመጨረሻም በራስጌው የትምህርት ሚኒስቴር አርማ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሚክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል። ቀጥሎ ባለው ገጽ የመጽሐፉን ወጪ አሽፋፈን እና ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የታተመበትን ዓመተ ምህረት እና ማተሚያ ቤቱን የሚገልጽ ተጽፎ ይገኛል። ይህ መረጃ ከተጻፈበት ገጽ ቀጥሎ ባለው ከፊትና ከጀርባ ማውጫ ከአንደኛ ሳምንት እስከ ሶስተኛ ሳምንት ተጽፎ ይገኛል። ከማውጫው ገጽ ቀጥሎ ባለው ገጽ መግቢያ ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች የሚል አምስት ነጥብ የያዘ መሰረታዊ መርሆች ተጽፈዋል። በቀጣይ ገጽ ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጽሐፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት የሚችሉባቸው አጠቃላይ መስፈርቶች ቀርበዋል። በቀጣይ ገጽም የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ በማለት ከስሩ የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች) በማለት ከተጻፈው ስር በመጽሐፉ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆመ ክፍሎች ባሉተ ጥቂት ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ መሆናቸውን ብዙዎቹ ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ መገኘታቸውን ይገልጻል።

በመቀጠልም ምልክቶቹም የጆሮ ምልክት የሚታይበት ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ፣ እጅን በማጣመር ወይንም የመጨባበጥ ምልክት ቃላትን በማንበብና ወደ ተለያዩ አሀዶች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ስርዓት እንዲጽፉ የሚያደርጋቸው ሲሆን መጽሐፍ የማንበብ ምልክቱ ህጻናት ዓረፍተነገሮፍን፣ አጫጭር ተረቶችን (ታሪኮችን) ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን እንዲያነቡ በማድረግ ላይ የሚያተኩር መሆኑን እና የቁልፍ ምልክት ክፍል ደግሞ አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም እንዲሁም የቃላቱን ፍቺ ከአገባባቸው ፈልጎ በማግኘት ስልት (ዘዴ) ላይ ማተኮሩን የሚገልጽ በመጨረሻም የመጻፍ ወይም የሚጽፍ እጅ ምልክት ክፍሉ ቃላትን፤ ዓረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን በመጻፍ ላይ እንደሚያተኩር የሚገልጽ፤ ልጆች በክፍል ውስጥና ወላጆች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንዳለባቸው ቀርቧል።

በዚህ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ገጾች አሉ። ሰላሳ ሳምንቶች ያሉት ሲሆን አርባ አምስት ምንባቦች ይገኛሉ። በምንባቦቹ ስር የተደለደሉ የትምህርት ይዘቶችና ጥያቄዎች ይገኛሉ። እነዚህ ይዘቶችና ጥያቄዎች ወይም መልመጃዎች በስድስት ክፍሎች የተደለደሉ ሲሆኑ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ በየደረጃው የንባብ ቃላትን የማጣመር፤ የመጻፍ፤ የማዳመጥና የንግግር ክሂል እንዲሁም

የስነልሳን፤ የስነጽሑፍ ይዘቶችና መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ሁሉም ምንባቦች በዝርው የተጻፉ ሲሆን በሁሉም ሳምንቶች ሁለት ንባብና አስር መልመጃዎች አሉ፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በመጽሐፉ ውስጥ ሰላሳ ሳምንቶች ያሉ ሲሆን በእያንዳንዱ  ሳምንት አራት ቀን የያዘ ሲሆን በየቀኑ የንባብ፣ የንግግር፣ የማዳመጥና የጽህፈት ክሂልን አካቶ ይዟል፡፡ ይህንንም በሰንጠረዥ መመልከት እንችላለን፡፡

**ሰንጠረዥ4.1፤- የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ መረጃ**

| የትምህርት ይዘቶች ሳምንት | የንባብ ክሂል | የንግግር | የማዳመጥ | የጽህፈት | ስነልሳን | ስነጽሑፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 2ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 3ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 4ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 5ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 6ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 7ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 8ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 9ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 10ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 11ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 12ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 13ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 14ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | ? |
| 15ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 16ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 17ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 18ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 19ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 20ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 21ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 22ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | - | - |
| 23ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 24ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | - |
| 25ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 26ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 28ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 29ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| 30ኛ ሳምንት | ? | ? | ? | ? | ? | ? |

አጠቃላይ የመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አራት መቶ ሀምሳ መልመጃዎች ይገኛሉ። ለዚህ ጥናትም ከዓላማው አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ የሚመለከት ነው። በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በአብዛኛው በስነልሳን ክፍል፣ በስነፍቾ፤ በንግግር፤ በጽህፈትና በስነጽሑፍ ውስጥ እናገኛለን። በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በመርሃ ትምህርቱ በተሰጣቸው ትኩረት አንጻርና መርሆችን ተከትለው ተደራጅተው ሊገኙ ይገባል። ስለሆነም አስቀድመን የመጽሐፉን አጠቃላይ መረጃ በሰንጠረዥ ለማየት እንሞክራለን።

**ሰንጠረዥ4.2፡- የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ መረጃ**

| ተ.ቁ. | መረጃዎች | |
|---|---|---|
| 1 | የተተኳሪው መጽሐፍ  የክፍል ደረጃ | 3ኛ ክፍል |
| 2 | የትምህርት ዘመን | 2009 ዓ.ም. |
| 3 | የገጽ ብዛት | 131 |
| 4 | የሳምንቱ ብዛት | 30 |
| 5 | የምንባብ ብዛት | 45 |
| 6 | የመልመጃዎች ብዛት | 450 |
| 7 | የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | 174 |
| 8 | የቀረቡባቸው ሳምንቶች ብዛት | 30 |

## 4.2. በ2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚደራጁ የትምህርት ይዘቶች በአግባቡ መካተት ይገባቸዋል፡፡ ይኸውም ይዘቶቹ የትኛው ከየትኛው ይዘት መቅደምና መከተል እንዳለበት እንዲሁም ይዘቶቹ በምን አይነት ሁኔታ መቅረብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ አደረጃጀታቸውም ከቀላል ወደ ከባድ፤ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሄድ እንዳለባቸው ሆኖ የድግግሞሹን ጥልቀት ሁኔታ የሚመለከት ይሆናል፡፡

ጥናቱ በዋነኛነት ተዋረዳዊ አደረጃጀቱን፣ ተከታታይነቱን፣ ተለጣጣቂነቱን፣ መስመራዊ ግንኙነቱን፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልቶችን የሚመለከት ይሆናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ትኩረት ከሆነው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱን አደረጃጀት ለመፈተሽ ይሞከራል፡፡

### 4.2.1. ከተከታታይነት አንጻር

ተከታታይነት ሲባል በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ብዛት የክፍል ደረጃ ውስጥ ተደጋግመው መቅረባቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም ከጥናቱ ትኩረት አንጻር በተተኳሪው ክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት በቀጣዮቹ ሳምንቶች ውስጥ ተደጋግሞ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ ተደጋግሞ መቅረብ አለበት ሲባል ግን በተመሳሳይ የቅለትና የክብደት ደረጃ መቅረብ አለበት ማለት ሳይሆን ጥልቀትና ስፋቱን እየጨመረ የሚሄድ መሆን አለበት ፡፡ ድግግሞሹም ልጆቹ ቀደም ሲል የተማሩትን የሰዋስው ይዘቶች በሚገባ እንዲገነዘቡ በማድረግና በቂ ዕውቀትን አግኝተው ወደ ቀጣይ ክፍል መሻገር እንዲችሉ የሚያግዝና ቀድሞ የተማሩትን ትምህርት የሚያጠናክር መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በመቀጠል በተተኳሪው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚገኙባቸውን ሳምንቶችና የድግግሞሽ መጠን ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ እንመለከታለን፡፡

ሰንጠረዥ4.3፡- በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚገኙባቸው ሳምንታት የድግግሞሽ መጠን

| በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የሳምንቱ ቁጥር | የተደገመበት ሳምንት መጠን | |
|---|---|---|---|
| ስነፍች | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ቃላትን ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ | 1፣2፣9፣11፣13፣16፣17፣21፣22፣24፣26፣27፣እና 28 | 12 | 40 |
| የቃላትና የሀረጋት ዐውዳዊ ፍች | 3፣12፣15፣20፣20፣ | 4 | 13 |
| ፊደላትን በማጣመር ቃል መመስረት | 1፣3፣4፣6፣9እና10 | 5 | 16 |
| የቃላት ቀጥተኛ(መዝገባዊ) ፍች መፃፍ | 3፣4 እና14 | 2 | 6 |
| የቃላት ተመሳሳይ ፍች መፃፍ | 5፣9፣14፣15፣19፣22፣25፣26እና29 | 8 | 26 |
| የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍች | 6፣24፣እና29 | 2 | 6 |
| ቃላትን በየምድባቸው መፃፍ | 7 | | |
| ስነ አገባብ | | - | - |
| ዐረፍተ ነገር መመስረት | 1፣4፣5፣6፣7፣11፣12፣16፣18እና24 | 9 | 30 |
| ዐረፍተ ነገር ማስተካከል | 15፣16 እና 23 | 2 | 6 |
| ዐረፍተ ነገሮችን ማሟላት | 8፣13፣19 እና 24 | 3 | 10 |
| የቃል ክፍሎችና ሙያ | 15፣17፣18፣19፣20፣23፣25 እና 29 | 7 | 23 |
| ስነ ምዕላድ | | - | - |
| ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ጋር ማጣመር | 2፣5፣8፣21፣24፣26፣29 እና 30 | 8 | 26 |
| ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ማዛመድ | 2 | 1 | 3 |
| ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል መነጠል | 2፣3፣5፣6፣7፣8፣10፣12፣13፣14፣15፣16፣17፣19፣20፣22፣25፣26 እና 28 | 18 | 60 |
| ቅጥያዎችን በመጨመር ባለ ቅጥያ ቃል መመስረት | 11 እና 16 | 1 | 3 |
| ተውላጠ ስሞች ዕርባታ | 3፣8እና 14 | 2 | 6 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ በብዛት የተደገመው 18 /60 በመቶ/ ስነምዕላድ ሲሆን ስነፍች ደግሞ 12 /40በመቶ/ በመደገም በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስነምዕላድ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉት ሳምንቶች በሁሉም ውስጥ ተካቷል፡፡ በስነምዕላድ ውስጥ ከሚገኙት ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል መነጠል የሚለው አስራ ስምንት ጊዜ እና ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ጋር ማጣመር የሚለው ዘጠኝ ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ የተውላጠ ስሞች ዕርባታ የሚለው ሁለት ጊዜ ተደግሞ ቀርቧል፡፡

ከስነፍች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ 12 /40 በመቶ/ የተደጋገመው ቃላትን ከፍቻቸው ማዛመድ ነው፡፡ የቃላትን ተመሳሳይ ፍች መጻፍ የሚለው በዘጠኝ ሳምንቶች ተደጋግሞ ተካቷል፡፡ ፊደላትን በማጣመር ቃል መመስረትና የቃላትና የሀረጋት አገባባዊ ፍች አምስት አምስት ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል፡፡ የቃላት ቀጥተኛ ፍችና የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍች ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል፡፡ ስነ አግባብ 9 /30 በመቶ/ ዐረፍተነገር መመስረት ተደግሞ የተካተተ ሲሆን የቃል ክፍሎችና ሙያ በ7 /23 በመቶ/ ተደግሟል፡፡ ዐረፍተ ነገር ማስተካከልና ማሟላት በአምስት ተደግሞ ተካቶ ቀርቧል፡፡

በ3ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች መካከል ቀደም ሲል እንደተገለጸው ስነምዕላድ ከፍተኛ የድግግሞሽ መጠን 18 /60 በመቶ/ ሲኖረው ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የድግግሞሽ መጠን ያለው ስነፍች 12/40 በመቶ/ ሲሆን በሶስተኛ ደረጃ ድግግሞሽ 9 /30 በመቶ/ ያለው ስነአገባብ እንደሆነ ታይቷል፡፡ በአንድ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በእኩል ደረጃ ድግግሞሽ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ነገርግን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች የድግግሞሽ መጠናቸው ተቀራራቢ ሊሆን ይገባል፡፡ በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ የሰዋስው ይዘቶች ለምሳሌ በስነ ምዕላድ ከፍተኛ የድግግሞሽ ልዩነት ያሳያል፡፡ ይህ ልዩነት ተማሪዎች እንዲረዱ ከሚታሰበው የዕውቀት መጠን በቂ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህን በማየት መማሪያ መጽሐፉ ሲዘጋጅ የተመጣጠነ ድግግሞሽ መጠን ቢኖረው የተሻለ ይሆን ነበር ለማለት ያስችላል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ተከታታይነትን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሐፉ ለአብነት ያህል እንደሚከተለው እንመልከት፡፡ ስነምዕላድን በተመለከተ 2ኛ ሳምንት በ3ኛ ቀን ገጽ7 ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በማጣመር

| ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለ ቅጥያ ቃል |
|---|---|---|
| በሬ | ዎች | በሬዎች |
| ዶሮ | ዎች | ዶሮዎች |
| አውሬ | ዎች | አውሬዎች |

በቀጣዩ ሳምንት ደግሞ ይህንኑ የሰዋስው ይዘት ስነምዕላድን በ5ኛ ሳምንት በገጽ18 ላይ ዋናውን ቃልና "ኦች" የሚለውን ቅጥያ በማጣመር ቅጥያ ያለው ቃል እንዲመሰርቱ ቀርቧል።

| ተ.ቁ. | ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለቅጥያ ቃል |
|---|---|---|---|
| 1. | ቤት | ኦች | ቤቶች |
| 2. | ልጅ | ኦች | ልጆች |
| 3. | ልብስ | ኦች | ልብሶች |

ስነምዕላድን በተመለከተ አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ሰላሳ የትምህርት ሳምንታት ውስጥ በአስራ ስምንቱ ሳምንታት ውስጥተደጋግሞ እናገኛለን። ከላይ ለአብነት ካነሳናቸውገጾች በተጨማሪ በገጽ 23፣ 26፣ 27፣ 30፣ 34፣ 38፣ 46፣ 48፣ 51፣ 53፣ 55፣ 57፣ 66፣ 67፣ 72፣ 87፣ 89፣ 91፣ 94፣ 96፣ 105፣ 109፣ 112፣ 117፣ 120፣ 122፣ 125፣ እና 129 በእነዚህ ገጾች የስነምዕላድን ይዘት በድግግሞሽ እናገኛለን።ስነፍች ስንመለከት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሌሎች የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተለያየ መጠን በተለያዩ ሳመንታት ተደጋግመው እናገኛለን።

ለአብነት ያህል ቃላትን ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን ገጽ አንድ

- ጤነኛ　　　ሀ- በአየር የሚተላለፍ የሚያስል በሽታ
- ጉንፋን　　　ለ- በበሽታ ያልተያዘ
- ወረርሽኝ　　　ሐ- በአንድ አካባቢ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃ በሽታ
-

2ኛ ሳምንት 2ኛ ቀን ገጽ 6

– ፀናበት ሀ- ቶሎ ቶሎ ያቃስታል
– ያቃስታል ለ- ተፈወሰ
– እንክብካቤ ሐ- እገዛ ማድረግ
– ዳነ መ- በረታበት

ስነፍችን በሚመለከት አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረበው ሰላሳ ሳምንታት ውስጥ አስራ ሶስቱ ሳምንታት ውስጥ ተደጋግሞ እናገኛለን። ከላይ ለምሳሌ ካነሳናቸው ገጾች በተጨማሪ በገጽ 33፣ 50፣ 63፣ 68፣ 89፣ 92፣ 96፣ 104፣ 110፣ 114፣ 116፣ 118፣ 121 እና 131 ላይ ተደጋግሞ ቀርቧል። ስነአገባብን በተመለከተ ከ1ኛ ሳምንት እስከ ሀያ ዘጠነኛ ሳምንት ድረስ ተደጋግሞ ቀርቧል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ በመነሳትና በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተደረገው ፍተሻ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አንዱ ካንዱ የመበላለጥና የመጠጋጋት መጠኑ ተቀራራቢ በመሆኑ የተከታታይነት ችግር እንደሌለው ለማስተዋል ተችሏል።

### 4.2.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር በመጠኑ ቢመሳሰልም የተወሰነ ልዩነት አለው።ተለጣጣቂነት የትምህርት ይዘቶች ተደጋግሞ መምጣት ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን ተደጋግሞ የሚመጣው የትምህርት ይዘት ቀደም ሲል ከቀረበው የትምህርት ይዘት ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ የመምጣት ሁኔታን የሚገልጽ ነው። ይህም ይዘቶች በየሳምንቱ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደገ የሚሄድ ዓይነት መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይዘቶቹ ሲደራጁ የድግግሞሽ ሁኔታ ጥልቀትና ክብደት እየጨመረ መሆን አለበት። ከዚህ ቀጥለን በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው የተለጣጣቂነት ሁኔታ እንደሚከተለው ይፈተሻል።

በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ በተከታታይነት ስር ለማየት እደተሞከረው በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንፃር በ2ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን ገጽ6 ላይ “ቅጥያን ከዋናው ቃል ነጥሉ” በሚል ትዕዛዝ የቀረበ ሲሆን በ4ኛ ሳምንት በ3ኛ ቀን በገጽ15 ላይ “-ኣት” የሚቀጠልባቸውን ቃላት መርጠው እንዲያጣምሩ ያዛል። በመቀጠልም በ5ኛ ሳምንት በ20ኛ ቀን በገጽ18 ላይ ዋናውን ቃልና “-ኦች” የሚለውን ቅጥያ በማጣመር ቅጥያ ያለው ቃል እንዲመሰርቱ የሚያዝ ነው። በ6ኛው ሳምንት በ3ኛው ቀን በገጽ23 ላይ ዋናውን ቃልና ቅጥያውን

ነጥለው እንዲጽፉ ያዛል። በ9ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 34 ላይ ቃላትን ከራሳቸው ፈልገው “-ዎች” ወይም “-ኦች” ከሚሉት ቅጥያዎች ጋር በማጣመር ወደ ብዙ ቁጥር እንዲለውጡ እና በ21ኛ ሳምንት በ3ኛ ቀን በገጽ 91 ላይ “-ኤ” ወይም “-ኣችን” የሚሉ ቃላት ያሉባቸው አምስት አምስት ቃላት እንዲፅፉ በ26ኛ ሳምንት በ1ኛ ቀን በገጽ 98 በተሰመረባቸው ቃላት ላይ ተስማሚ ቅጥያ በመጨመር ዐረፍተ ነገሮቹን እንደገና እንዲፅፉና በ30ኛው ሳምንት በ1ኛው ቀን በገጽ 129 ላይ ባለንብረትነትን አመልካች በሆኑ በ-ዋ፣ -ኡ፣ -ህ፣ -ሽ፣ -ኦች፣ -ዎች፣ -ኣት፣ እነዚህን ቅጥያዎች ከቃል ጋር እንዲያጣምሩ ያዛቸዋል። ስለሆነም በዚህ ስለምዕላድ በኩል ያሉትን ይዘቶች ስንመለከት በዓይነትና ቅርጽ በመቀያየር መደራጀቱ በተሻለ ሁኔታ ከሳምንት ሳምንት የሽግግር ተለጣጥቆነት የተሻለ እንደሆነ ተመላክቷል።

ስነ-ፍችን አስመልክቶ የቀረቡት መረጃዎች ፍተሻ ሲመረመር በ1ኛ ሳምንት በ1ኛ ቀን በገጽ 1 ላይ ቃላት ከሚለው ስር “በ ”ሀ” ምድብ ለቀረቡት ቃላት በ ”ለ” ምድብ ከቀረቡት ፍቻቸው በመምረጥ አዛምዱ፤” የሚለውና በ3ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 10 ላይ ቃላት ከሚለው ስር ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ፤ በአራተኛ ሳምንት በአንደኛው ቀን በገጽ 13 ላይ ቃላት ከሚለው ስር በቡድን በመወያየት ለቃላቱ ፍቻቸውን እንዲጽፉ፤ እና ቃላት ምስረታን ስንመለከት 1ኛ ሳምንት 2ኛ ቀን ከገጽ 2 ላይ ፊደላትን በማጣመር ቃል እንዲመሰርቱ፣ በ10ኛ ሳምንት በ3ኛ ቀን በገጽ 39 ላይ ሆሄያትን በማጣመር ባለ አራትና ባለ አምስት ፊደል ቃላት እዲመሰርቱ፣ በ15ኛው ሳምንት በ1ኛ ቀን በገጽ 59 በቃላቱ የቢንጎ ጨዋታ በመጫወት እንዲለማመዱ፣ በ17ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 71 ከተሰጡት ቃላት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ በባዶ ቦታ ላይ እንዲያስገቡ፣ በ19ኛው ሳምንት በ2ኛው ቀን በገጽ 80 ላይ የእርሻ መሳሪያ ክፍል ስያሜዎችን ከስዕሉ ጋር እንዲያዛምዱ በማድረግ፣ በ20ኛው ሳምንት በገጽ 84 ላይ አዝርዕቱን በየምድባቸው እንዲፅፉ በማድረግበመማሪያ መጽሐፉ የስነፍችን አደረጃጀት በተመለከተ ከሳምንት ሳምንት ከፍ እያለ (ከቀላል ወደ ከባድ) የሄደ በመሆኑ ተለጣጣቂነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል።

ስነ-አገባብን በተመለከተ በ1ኛ ሳምንት በ4ኛ ቀን ገጽ4 ላይ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ በ4ኛው ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 14 ላይ በቡድን በመሆን ዓረፍተነገር እንዲሰሩ ያዛል። በ7ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 26 ላይ በቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያዛል። በ8ኛ ሳምንት በ1ኛ ቀን በገጽ 29 ላይ አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ያዛል፣ በ13ኛ ሳምንት 2ኛ ቀን በገጽ 52 ላይ ተገቢውን ቃል/ሐረግ መርጠው

ዓረፍተ ነገሮቹን እንዲያሟሉ እና በ20ኛው ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 86 ላይ የስምና የግስ ገላጭ ያላቸውንና ስርዓተ ነጥባቸው የተሟላ አምስት ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት እንዲፅፉ ያዛል። በ21ኛው ሳምንት በ2ኛው ቀን በገጽ 90 ላይ ለደኖች መጨፍጨፍ ምክንያት የሆኑ ነገሮች እንዲገልፁ ያዛል። በ23 ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 99 ላይ በየቀኑ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ከአምስት እስከ አስር የሚደርሱ ዓረፍተ ነገሮች ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው እንዲፅፉ ያዛል። በ25 ሳምንት በ4ኛ ቀን በገጽ 110 ላይ የቃላትን ቅደም ተከተል በማስተካከል ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው ዓረፍተ ነገሮችን እንደገና እንዲፅፉ ያዛል። በ28 ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 121 ላይ "አርሶ አደር ብሆን ማምረት የምፈልጋቸው የምርት ዓይነቶች" በሚል ርዕስ ከአምስት እስከ አስር በሚደርሱ ዓረፍተ ነገሮች አንደ አንቀጽ እንዲፅፉና በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥም ተገቢ ስርዓተ ነጥብ እንዲያስገቡ ያዛል። መልመጃዎቹን ስንመለከት ከቅለት ወደ ክብደት ደረጃ ያሉ ሲሆን እያደጉ የመምጣት ሁኔታ ይታይባቸዋል፣ ማለትም በቀረበላቸው ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ከማድረግ በመጀመር ተገቢ ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አምስት ዓረፍተ ነገሮች እንዲፅፉ ያዛል። ከዚያም የፃፉትን በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ፣ የትምህርት ቤታቸውን የኳስ ሜዳ በመመልከት ያዩትን በአስር ቃላት ጽፈው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያዛል። "የእናት ምክር" የሚለውን ጽሑፍ በራሳቸው አባባል በአምስት ዓረፍተ ነገሮች እንደገና ጽፈው ለመምህራቸው እንዲያሳዩ ያዛል፣ "ታታሪ አርሶ አደር" በሚል ርዕስ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አንድ አንቀጽ ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያዛል። ስለዚህ በየሳምንቱ ያሉት ከቅለት ወደ ክብደት ደረጃ የመጡ በመሆናቸው የተለጣጣቂነት ችግር የለባቸውም ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ወስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ክብደትና ስፋታቸውን እየጨመሩ የተደራጁ በመሆናቸው ተለጣጣቂነት አላቸው።

### 4.2.3. መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት

መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት የሚባለው በስርዓተ ትምህርት ውስጥ የተቀረጹትን የትምህርት ይዘቶች ግንኙነት የሚያመላክት ነው። በአንድ ክፍል ውስጥ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች የእርስ በርስ መደጋገፍና አንዱ የሌላውን ይዘት በመደገፍ ለማስተማሪያነት ሲውልና በዚሁ ሁኔታ ተደራጅቶ ሲገኝ መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት በመባል

ይታወቃል፡፡ለአብነት ያህል በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀትን ከተለያዩ የትምህርት ይዘቶች የእርስ በርስ መደጋገፍ ምን እንደሚመስል ለማየት እንሞክራለን፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ የንባብ ክሂል፣ የጽህፈት ክሂል፣ የንግግር ክሂልና የስነጽሑፍ ይዘት ጋር አንዱ ሌላውን ለማስተማር ተግባር ተደራጅቶ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሰዋስው ይዘት እርስ በርሳቸው መስመራዊና ኡደታዊ ሂደትን ጠብቀው ዕድገት እያሳዩ አንዱ የሰዋስው ይዘት ሌላውን የሰዋስው ይዘት እድገት እንዲኖረው እየደገፈና እያዳበረ የመጣበት ሁኔታ ለማየት ተችሏል፡፡ይህንንም በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥበሚከተለው መልኩ ለማየት እንሞክራለን፡፡

በገጽ አንድ ላይ “አስቴር በሀኪም ቤት”፣ ገጽ 4 ላይ የአካባቢ መበከል፣ ገጽ7 ላይ “በጤና መኖር”፣ ገጽ 9 ላይ በሽታን መከላከል፣ በገጽ 11 ላይ ልጆች ተከተቡ፣ እነዚህን ምንባቦች በምንመለከትበት ጊዜ ከሳይንስ ትምህርት ጋር እርስ በርስ የመደጋገፍ ሁኔታ መኖሩ ይታያል፡፡በተጨማሪም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ የንባብ ክሂል፣ የማዳመጥ ክሂል፣ የንግግር ክሂል እና የጽህፈት ክሂል የሰዋስው ይዘት መደጋገፍና ግንኙነት ሲታይ ከመጀመሪያው የትምህርት ሳምንት በመደጋገፍ ቀርበዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የእርስበርስ መስመራዊ ግንኙነት ሁኔታ ሲታይ በአብዛኛው አንዱ ሂደት ሌላውን እያሳደገና እየደገፈ በመሄድ ሁኔታ መስመራዊ አደረጃጀቱን የጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ከዚህ በመነሳት በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች ጋር እና እርስ በርስ ካላቸው ትስስር መስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት ጥሩ የሚባል እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ሌሎች ይዘቶች ከሰዋስው ይዘት ጋር ያላቸው መስመራዊና ኡደታዊ ግንኙነት በሚመለከት የንባብ ክሂል፣ የጽህፈት ክሂል፣ የንግግር ክሂልና ስነጽሑፍ ከሰዋስው ይዘት ጋር መስመራዊና ኡደታዊ ግንኙነት አላቸው፡፡

### 4.2.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንጻር

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት የታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት የሚያሳይ የሰዋስው ማብራሪያ ወይም ገለጻ ለተማሪዎች ሳይቀርብ በቀረበላቸው ምሳሌ መሰረት በመታገዝ የሚሰሩበት መንገድ ነው፡፡ የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሊደራጁ ይችላሉ፡፡ በተተኳሪው በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ

የሰዋስው ትምህርትይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀቱ ምን እንደሚመስል ከመማሪያ መጽሐፉ ቀጥለን እንመለከታለን።

በመማሪያ መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር ተደራጅተው ይገኛሉ። አስቀድመን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት በሚመለከት ከመጀመሪያው ሳምንት ጀምረን እናያለን። በ1ኛ ሳምንት በ1ኛ ቀን በገጽ 1 ላይ ቃላት በሚለው ስር በ "ሀ"ምድብ ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ከቀረቡት ፍቻቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ የሚያዝ ትዕዛዝ አለ። ከትዕዛዙ በመቀጠል በ "ሀ" ረድፍ አራት ቃላት በ "ለ" ረድፍ አራት ሀረጋት ተሰጥተዋል። ነገር ግን አስቀድሞ ፍች ምን እንደሆነ የተሰጠ ገለጻ የለም። በዚሁ ሳምንት በሁለተኛ ቀን በገጽ 3 ላይ መፃፍ ከሚለው ስር በአካባቢያቸው ስለሚዘወተሩ የቤት አሰራሮች ተገቢ ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም አምስት ዓረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ ያዛል። ነገር ግን ስለስርዓተ ትምህርት ምንም ዓይነት ገለጻ አልተቀመጠላቸውም። በተመሳሳይ ሁኔታ በ2ኛ ሳምንት 3ኛ ቀን በገጽ 7 ላይ ማጣመር ከሚለው ስር ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በማጣመር ክፍት ቦታውን እንዲሞሉ ትዕዛዝ ቀርቧል። ነገር ግን ስለ ቅጥያ ምንነት አስቀድሞ የተሰጠ ገለጻ ወይም ማብራሪያ የለም።

በ6ኛ ሳምንት በ4ኛ ቀን በገጽ 24 ላይ ቃላት በ "ሀ" የተገለጹትን ቃላት በ "ለ" ስር ከተዘረዘሩት ተቃራኒ ቃላት ጋር እንዲያዛምዱ ቀርቧል። ነገር ግን ቀደም ብሎ ስለ ተቃራኒ ቃላት ምንነት የሚገልጽምንም ዓይነት የቀረበ የለም። በተመሳሳይ በ13ኛ ሳምንት በ4ኛ ቀን በገጽ 54 ላይ ቃላት ከሚለው ስር ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ያዛል። ሆኖም አስቀድሞ ግን ስለ አገባባዊ ፍች የተሰጠ ማብራሪያ የለም። በ15ኛው ሳምንት በ3ኛ ቀን በገጽ62 ላይ መነጠል ከሚለው ስር በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ስሞችና ግሶችን ለይተው በማውጣት እንዲጽፉ ያዛል። ነገር ግን ስለ ስምና ግስ አስቀድሞ የተሰጠ ገለጻወይም ማብራሪያ የለም።በተመሳሳይም በ18ኛው ሳምንት በ3ኛ ቀን በገጽ76 ላይ መነጠል ከሚለው ስር ስሞችን፣የስም ገላጮችን፣ የግስ ገላጮችንና ግሶችን ለይተው እንዲያመለክቱ ታዟል። አንድ ምሳሌ ተሰጥቶ ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ተሰጥተዋል። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

| ተ.ቁ. | ምሳሌ | የስምገላጭ | ስም | የግስ ገላጭ | ግስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጎበዙ አርሶ አደር በፍጥነት መጣ | ጎበዙ | አርሶ አደር | በፍጥነት | መጣ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ጠይሟ ሰልጣኝ በሩጫ መጣች | | | | |
| 3 | ረጅሙ ዛፍ ዛሬ ተቆረጠ | | | | |
| 4 | አጭሯ መምህርት ትናንትና ሄደች | | | | |

አስቀድሞ ግን ስለነዚህ የቃል ክፍሎች የሚገልጽ ምንም ማብራሪያ ያልተሰጠ ሲሆን ምሳሌውን አይተውና በምሳሌው ታግዘው እንዲሰሩ የተሰጠ ነው።

በ19ኛ ሳምንት በ4ኛ ቀን በገጽ 82 ላይ መጻፍ ከሚለው ስር “ታታሪ አርሶ አደር ብሆን“ በሚል ርዕስ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አንድ አንቀጽ እንዲጽፉና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያዛል። ነገር ግን ስለ አንቀጽ ምንነትና አጻጻፍ የተገለጸ ምንም ነገር የለም። በ13ኛ ሳምንት በ4ኛ ቀን በገጽ131 ላይ መጻፍ ከሚለው ስር “የግብይት ስርዓት“ የሚለውን ምንባብ ከሶስት እስከ አምስት በሚደርሱ ዓረፍተ ነገሮች አሳጥረው እንዲጽፉ ያዛል። ነገር ግን እንዴት አሳጥረው መጻፍ እንዳለባቸው የሚገልጽ ነገር የለም።

### 4.2.5. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀትንስንመለከት ተማሪዎች አስቀድሞ ስለሚማሩት ቋንቋ ስርዓት የሚያሳውቅ ገለጻ ይቀርብላቸዋል። ከገለጻው በመነሳት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት ተረድተው በተግባር ላይ እንዲያውሉ ይደረጋል። ይህ ደግሞ ሰዋስዋዊ ህግጋትን አውቀው በቀላሉ እንዲረዱ ያደርጋል። በተጨማሪም በምሳሌዎች ታግዞ መቅረብ ይኖርበታል። ስለዚህ የዚህ አደረጃጀት ስልት በምሳሌ በሚገባ ታግዞ ከቀረበና ገለጻ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ገለጻና ምሳሌ መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎችን እየሰሩ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት እንዲረዱ የሚያደርግበት ዘዴ ነው። በታላሚው መማሪያ መጽሐፍውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ይዘቶች ለአብነት የተወሰኑትን ወስደን እንመለከታለን።

በ1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን በገጽ 1 ላይ አስቴር በሀኪም ቤት የሚል ምንባብ ቀርቧል። ከዚያ በመቀጠል ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በ3ኛ ቀን በገጽ 3 ላይ በሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመጠቀም ባለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃሎች መስርቱ።

| ፊደላት | ባለሁለት ፊደል ቃል | ባለሶስት ፊፊደል ቃል |
|---|---|---|
| አ በ ሰ ለ | አለ | አበሰ |
| ደ ሳ ባ ከ | | |
| ጠ ጣ ጨ ጫ | | |

በተጨማሪም በ3ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን ገጽ 9 ላይ የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጻፉ። ከዚህ ትዕዛዝ ቀጥሎ ምሳሌ ተሰጥቷል፤ በምሳሌው መሰረት አራት ጥያቄዎች እንዲሰሩ ቀርበዋል። በተጨማሪም በ4ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን ማጣመር ከሚለው ስር በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ፊደሎች በማጣመር በለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃላት እንዲመሰርቱ አስቀድሞ በምሳሌ የታገዘ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ነው። ለአብነት ያህል

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ጠ | ዋ | ጣ | ተ | መ | ታ | ማ | በ | ጨ | ባ | ጫ |

ባለሁለት ፊደል ቃል ባለሶስት ፊደል ቃል

ምሳሌ - መጣ - ጨበጠ

በተጨማሪም በ4ኛ ሳምንት በ2ኛ ቀን በገጽ 14 ላይ በቡድን በመሆን ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ የተሰጠ መልመጃ አለ። መልመጃውም በምሳሌ ታግዞ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች እንዲሰሩ አምስት ቃላትና ሀረጋት ተሰጥተዋል። ለአብነት ያህል፤-

በቡድን በመሆን ዓረፍተ ነገር ስሩ፤

ምሰሌ - መረዳዳት- ጥሩ ጎረቤታሞች በመረዳዳት ይሰራሉ።

1 - ወዳጅነት 2 - መከባበር 3 - መተማመን 4 - አብሮ መኖር 5 - መቻቻል

በ10ኛው ሳምንት 2ኛ ቀን ገጽ38 ላይ መነጠል ከሚለው ስር ዋናውን ቃል ከቅጥያ ነጥለው እንዲያሳዩ የተሰጠ መልመጃ አለ። መልመጃውም በምሳሌ ተብራርቶ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች እንዲሰሩ አምስት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል። ለአብነት ያህል-

ዋናውን ቃል ከቅጥያ ነጥላችሁ አሳዩ።

ምሳሌ - ወርቾ - ዋና ቃል - ወር፣ ቅጥያ ፡- -ኦች

– ሰፈራዎች - ዋና ቃል - ሰፈራ ፣ ቅጥያ -ዎች

1 - ተማሪዎች 2 - ወንዶች 3 - ተራራዎች 4 - እነሙሉ 5 - አመታት

በ11ኛው ሳምንት ገጽ 43 ላይ በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስሞችንና ግሶችን ለይተው በማውጣት እንዲጽፉ የተሰጠ መልመጃ አለ። መልመጃውም በምሳሌ ታግዞ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ አራት ዓረፍተ ነገሮች ተሰጥተዋል። በ12ኛ ሳምንት ገጽ 46 ላይ መነጠል ከሚለው ስር በምሳሌ መሰረት ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በመነጠል እንዲጽፉ ምሳሌ ቀርቧል። በምሳሌው መሰረትም እንዲሰሩ ቃላት ቀርቧል።

በ15ኛው ሳምንት በገጽ 63 ላይ መጻፍ ከሚለው ስር በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ቅደም ተከተል በማስተካከል ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እንዲያስገቡ ምሳሌ ተሰጥቷል። በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ አምስት የሚስተካከሉ ዓረፍተ ነገሮች ተሰጥተዋል።

ለአብነት ያህል ፤- ሄደች ልጅ አጭሯ አሁን

አጭሯ ልጅ አሁን ሄደች።

1. ዛሬ የቀይ ዳማዋ መጣች ወጣት
2. ገዛ ባለሱቅ መኪና ወጣት

በ16ኛው ሳምንት በገጽ 66 ላይ ማንበብ ከሚለው ስር ምንባቡን መሰረት በማድረግ አራት ጥያቄዎችን በጽሑፍ እንዲመልሱ ተሰጥቷቸዋል። በ19ኛ ሳምንት ገጽ 79 ላይ መነጠል ከሚለው ስር የቀረበው መልመጃ በምሳሌ ታግዞ የቀረበ ነው። በምሳሌው መሰረት የሚሰሩ አራት ጥያቄዎች

ይገኛሉ። በ22ኛ ሳምንት ገጽ 93 ላይ ዕደ-ጥበበትና ውጤታቸው በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቧል። በምንባቡ መሰረት የሚሰሩት አራት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በ23ኛው ሳምንት በገጽ 98 ላይ ማጣመር ከሚለው ስር በተሰመረባቸው ቃላት ላይ ተስማሚ ቅጥያ በመጨመር ዓረፍተ ነገሮቹን እንደገና እንዲጽፉምሳሌ የቀረበላቸው ሲሆን በምሳሌው መሰረትም እንዲሰሩ አራት ጥያቄዎች ተሰጥቷቸዋል።

ከ24ኛው ሳምንት እስከ 30ኛው ሳምንት በእያንዳንዱ መልመጃ ላይ በምሳሌው ታግዘው እንዲሰሩ የቀረቡ መልመጃዎች እንደተሰጣቸው በተተኳሪው መጽሐፍ የተደረገ የሰነድ ፍተሻ ለማየት ተችሏል።

በአጠቃላይ በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተደረገ ፍተሻ የሰዋስው ይዘቶችን አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከሚለው አደረጃጀት ስልት ጋር በጥምረትተደራጅተው መገኘታቸው ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት አመጣጥኖ በመቅረቡ በጣም ጥሩ የሆነ አደረጃጀት እንዳለው ማየት የተቻለ ሲሆን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በሰንጠረዥ ይቀርባል።

ሰንጠረዥ4.4፡- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

| ተ.ቁ. | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበ መልመጃ | 66 | 38 |
| 2 | አጠቃላይ ወደ ከዝርዝር የቀረበ መልመጃ | 58 | 33 |
| 3 | ምሳሌና ገለጻ ሳይሰጥ የቀረበ መልመጃ | 50 | 28 |
| 4 | አጠቃላይ የሰዋስው መልመጃ | 174 | 100 |

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ገለጻወይም ማብራሪያ ሳይሰጥ በምሳሌበመደገፍ የቀረቡ መልመጃዎችን ስንመለከት በገጽ1፣2፣3፣7፣8፣9፣10፣11፣13፣14፣15፣18፣21፣22፣23፣26፣27፣29፣30፣34፣35፣38፣39፣40፣41፣43፣46፣47፣48፣49፣51፣53፣54፣55፣57፣58፣59፣63፣65፣66፣67፣71፣72፣75፣76፣79፣81፣82፣86፣87፣89፣90፣91፣98፣99፣103፣105፣106፣112፣114፣117፣120፣122፣125፣127፣129 እና 131 ላይ ተካተዋል።

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት (አሰቀድሞ ስለሚማሩት) ቋንቋ ስርዓት የሚያሰውቅ ገለጻ አስቀድሞ ይቀርብላቸዋል፡፡

በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀትን ስንመከት ለመልመጃዎቹ የቀረበ ገለጻና ማብራሪያ ሳይሆን ምንባብ ተሰጥቶ በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ ወይም በቃል እንዲመልሱ የቀረቡ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነርሱም በገጽ፡- 2፣3፣4፣6፣7፣8፣10፣11፣12፣13፣15፣16፣18፣20፣22፣23፣24፣26፣27፣28፣30፣32፣34፣35፣36፣38፣40፣42፣44፣49፣52፣54፣56፣58፣60፣63፣66፣67፣75፣81፣85፣90፣91፣94፣96፣100፣104፣108፣110፣112፣114፣116፣118፣121፣125፣127እና 131 ላይ ተካተው እናገኛለን፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ምሳሌና ገለጻ ያልተሰጣቸው ወይም በምባቡ መሰረት እዲሰሩ ያልቀረቡ መልመጃዎችም አሉ፡፡ እነርሱም በገጽ 1፣ 6፣ 16፣ 19፣ 21፣ 23፣ 25፣ 28፣ 32፣ 33፣ 36፣ 37፣ 41፣ 46፣ 50፣ 55፣ 63፣ 66፣ 72፣ 76፣ 79፣ 92፣ 96፣ 98፣ 106፣ 108፣ 114፣ 118፣ 121፣ 126፣ 127 እና 131 ላይ ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት 66(38 በመቶ) መሆኑንና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቱ 58 (33 በመቶ) በሆነ መልኩ መደራጀታቸውን ከሰነድ ፍተሻው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ጥሩ የሆነ አደረጃጀት እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡

## 4.3. የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍና ለዚሁ ክፍል ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው መጣጣም፤

መርሀ ትምህርት ተማሪው የሚማርበትን እና መምህሩ የሚያስተምርበትን አቅጣጫ የሚያመላክት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን ዝግጅት የሚወስን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚረዳ የፈተና እና የግምገማ ሂደቶችንየሚያሳይ ሰነድ ነው፡፡በመሆኑም ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ስለ ሰዋስው የቀረበውን ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ ሰዋስው አለው፡፡ ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ሰዋስው ሁልጊዜ የትምህርቱ አካል ይሆናል፤ ነገር ግን በትምህርቱ ይዘት ውስጥ ተቀናጅቶ ይቀርባል፡፡ ይህ ማለት መምህሩና የትምህርት መሳሪያው (መጽሐፍቱ) ተማሪዎች ቋንቋውን በትክክል እንዲጠቀሙ ያዛል፤ ሆኖም ተማሪዎቹ የተለያዩ የቃል ክፍሎችን በሚማሩበት ጊዜ የሰዋስው ትምህርት የሚመለከት በተናጠል ራሱን የቻለ ትምህርት

አይኖርም። በመሆኑም ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ሰዋስው በቃላት አወቃቀር መልመጃዎች፤ በቃላት ትርጉም እና በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውስጥ ተቀናጅቶ ይቀርባል።በሌላ አነጋገር ሰዋስው በቃላዊ ልምምድ፤ በንባብና በጽህፈትክሂል ውስጥ ይተገበራል።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ቀጥለን እንመልከት።

የተተኳሪው ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በሳምንትና በቀን የተከፋፈለ (30 ሳምንታትና 131 ገጾች ሲኖሩት) ለዚሁ የክፍል ደረጃ የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ደግሞ በሁለት ወሰነ ትምህርት ተከፍሎ ይገኛል።በመማሪያ መጽሐፉና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተጣጥመው መቅረብ አለመቅረባቸውን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን።በሁለቱም ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከዚህ ቀጥለን በሰንጠረዥ እንመልከት።

ሰንጠረዥ4.5.፡- የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ-መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው መጣጣም

| ተ.ቁ. | ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ | በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስነ- ፍች | ቃላትን ከቀረቡ ፍቻቸው ማዛመድ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላትና የሀረጋት አገባባዊ ፍች | ✓ | ✓ |
| | | ፊደላትን በማጣመር ቃል መመስረት | ✓ | ✓ |
| | | የቃላት ተመሳሳይ ፍች መጻፍ | ✓ | ✓ |
| | | የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍች መጻፍ | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን በየምድባቸው መጻፍ | ✓ | ✓ ✓ |
| | | ዓረፍተ ነገር መመስረት | ✓ | ✓ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ስነ-አገባብ | ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከል መመስረት | ✓ | ✓ |
| | | ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት | ✓ | ✓ |
| | | የቃል ክፍሎችና ሙያ | ✓ | ✓ |
| 3 | ስነ-ምዕላድ | ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ጋር ማጣመር | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን በምዕላዶች መነጣጠል | ✓ | ✓ |
| | | ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ማዛመድ | ✓ | ✓ |
| | | ቅጥያዎችን በመጨመር ባለ ቅጥያ ቃል መመስረት | ✓ | ✓ |
| | | የተውላጠ ስሞች ዕርባታ | ✓ | ✓ |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደተሞከረው በመማሪያ መጽሐፉና ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው ነው። በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ እና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በጣም የተጣጣሙና በዝግጅት ወቅትም ትኩረት ተሰጥቶት መርሀ ትምህርቱን መነሻ ተደርጎ መዘጋጀቱን ያሳያል። በመሆኑም ተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት መካከል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በሚመለከት ጥብቅ ቁርኝት እንዳላቸውና የተጣጣሙ መሆናቸውን መግለጽ ይቻላል።

በአጠቃላይ ብዙ ጠነካራ ጎን ቢታይበትም መማሪያ መጽሐፉ በሳምንቶችና በቀናት ሲከፈል መርሀ ትምህርቱ በወሰነ ትምህርት ብቻ መከፈሉ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጠንካራ የሆነ ትስስርና ዝምድና እንዳላቸው ከተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለመረዳት ተችሏል።

## 4.4. በ2009 ዓ.ም.በታተመው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መልመጃዎች ሲቀርቡ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው መስፈርቶች አሉ። እነርሱም ግልጽነት፣ ትክክለኛነት፣ ተገቢነት እና ተመጣጣኝነት የሚባሉ ናቸው። በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በምን ሁኔታ እንደተዘጋጁ ቀጥሎ እያንዳንዱን እንመልከት።

### 4.4.1. ከግልጽነት አንጻር

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ግልጽ በሆነ መንገድ ሊቀርቡ ይገባል። ምክንያቱም ተምሪዎቹም ሆነ መምህር,ራን መተግበር እንዲችሉ የቀረቡ ምንባቦች፣ ትእዛዞች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ግልጽነት ሊኖራቸው ይገባል። ተማሪዎቹ በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው፤ የማያወዛግቡና ግራ የሚያጋቡ መሆን የለባቸውም። ከዚህ በመቀጠል በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎችና ይዘቶች ከግልጽነት አንጻር እናያለን።

በ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ግልጽነት በሚመለከት እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል። በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ ትዕዛዞች፣ምሳሌዎችና ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ግልጽነት አላቸው። ነገር ግን አንዳንድ የግልጽነት ችግር መኖሩ ስለተስተዋለ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡

ሀ. **ከትዕዛዞች አንጻር**

በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ትዕዛዞች የግልጽነት ችግር የለባቸውም። ነገር ግን አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ መመሪያዎችም አሉ። ለአብነት ያህል በገጽ 25 በ7ኛው ሳምንት በ1ኛ ቀን ላይ ትዕዛዙን መመልከት ይቻላል።

ቃላትን መርጣችሁ በተገቢው ክፍት ቦታ አስገቡ፤

ሁል ጊዜ   ጥንታዊ   ማህበራዊ   ባህል፡

1.---------- በቀድሞ ጊዜ የነበረ

2.-------------- ልማድ

3.-------------- ዘውትር

4. -------------- የጋራ

መመሪያውን ስንመለከት ቃላቱን መርጠው በተገቢው ቦታ እንደያስገቡ ነው። ነገር ግን ቃላቱን የሚመርጡት ተመሳሳይ የሆነውን ነው  ወይስ ተቃራኒውን  ተማሪዎቹ የሚመርጡት እነርሱ

የሚፈልጉትን ብቻ ሊሆን ስለሚችል ግልጽነት ይጎድለዋል።በተጨማሪም በገጽ 56 ላይ በቡድን በመወያየት የቃላቱን ፍች እንዲጽፉ ያዛል። ነገር ግን የቃላቱን ፍቺ እንዲጽፉ ከማዘዝ ባለፈ ፍች የሚጽፉት ለቃላቱ ተመሳሳያቸውን ወይም አገባባዊ ፍቻቸውን እንደሆነ የተገለጸነገር ባለመኖሩ ግልጽነት ይጎድለዋል። በተመሳሳይም በገጽ 79፣ 98 እና 108 ላይ ግልጽነት የሌላቸው ትዕዛዞች አሉ። ከዚህ በመነሳት የተወሰኑ ትዕዛዛት ላይ የግልጽነት ችግር እንዳለባቸው ለማየት ተችሏል።

ለ. **ከምሳሌዎች ግልጽነት አንጻር**

በተተኳረው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ምሳሌዎች የግልጽነት ችግር እንደሌለባቸው በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ታይቷል።

ሐ. ከጥያቄዎች ግልጽነት አንጻር

በተተኳረው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ይዘት መልመጃዎች ከጥያቄዎች ግልጽነት አንጻር በተደረገው የሰነድ ፍተሻ አብዛኛው ጥያቄዎች የግልጽነት ችግር የለባቸውም። ነገር ግን ግልጽነት የሌለው የሚመስል ጥያቄ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተገኝቷል። በ19ኛው ሳምንት በ2ኛው ቀን በገጽ 80 ላይ የግልጽነት ችግር ያለው የሚመስልናተማሪዎቹ በቀላሉ ሊያውቋቸው የማይችሉ ስያሜዎች ቀርበዋል። እነዚህ ስያሜዎች ተማሪዎቹን ግራ የሚያጋቡ አይነት ይመስላሉ። እነርሱም ፤- የእርሻ መሳሪያ ክፍል ስያሜዎችን ከስዕሉ ጋር አዛምዱ።

| | |
|---|---|
| 1 - እርፍ | 6 - ማነቆ |
| 2 - ድግር | 7 - ቀምበር |
| 3 - ማረሻ | 8 - መዋጀ |
| 4 - ወገል | 9 - ምራን |
| 5 - መርገጥ | 10 - ሞፈር |

እነዚህ የእርሻ መሳሪያ ክፍል ስያሜዎች ተማሪዎቹ ዕለት ተዕለት የሚያገኟቸው ባለመሆኑ ግራ ሊያጋቧቸው ስለሚችሉ ከጥያቄዎች ግልጽነት አንጻር በአብዛኛው በጣም ጥሩ ቢሆንም እነዚህ ላይ ግን ጥያቄው ችግር እንዳለበት ከሰነድ ፍተሻው ለማየት ተሞክሯል፡፡

መ. **ማስታወሻ (ገለጻ) ከግልጽነት አንጻር**

በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበ ምንም ዓይነት ማስታወሻ ወይም ገለጻ እንዳልቀረበ በተደረገ የሰነድ ፍተሻ ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ምንባቦች ውስጥ በሚገባ ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊያነቡት በሚችሉት መንገድ መቅረቡ ታይቷል፡፡

ሠ. **ከዓላማ ግልጽነት አንጻር**

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ዓላማ አልተገለጸም፡፡ ነገር ግን በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ ከትምህርቱ ፍጻሜ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ዓላማ የቀረበው ከመርሀ ትምህርቱ መግቢያ ላይ ሳይሆን በሰስት በመክፈል ይኸውም ቃላዊ ክፍሎች (ማዳመጥና መናገር)፣ ማንበብ፣ መጻፍ በማለት በመለየት ተማሪዎች እንዲኖራቸው የሚፈለገውን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች አንድ ላይ በማስፈር ነው፡፡ አብዛኛዎቹ አላማዎች በግልጽ አቀራረብ ተቀምጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ አንዳንድ የአላማ ግልጽነት የጎደለው ታይቷል፡፡ ለአብነት ያህል በገጽ 54 ላይ የሚገኝ የማንበብ ክሂል ስር የተቀመጠው ዓላማ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ ተማሪዎቹን ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡

### 4.4.2. ከትክክለኛነት አንጻር

በታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ውስጥ ትክክለኛ የሰዋስው ህግጋት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቀርቦ ከተገኘ ትክክለኛነት ይባላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከትክክለኛነት አንጻር ያለውን ገጽታ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

በ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የታላሚውን የቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀመውን እውነተኛ የሰዋስው ህጎችን በይዘትነት እንደቀረቡ ከፍተሻው ለማየት ተችሏል፡፡ አንዳንድ ግልጽነት የጎደላቸው ይዘቶች ከመኖራቸውና

የሚያደናግሩ ይዘቶች በስተቀር የጎላ ችግር በመማሪያ መጽሐፉ የለም። በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ከትክክለኛነት አንጻር እንደ ክፍተት የታየው በገጽ 80 ላይ የቀረቡ የእርሻ መሳሪያ ክፍል ስያሜዎች ከስሩ ማዛመድ የሚለው ነው። ምክንያቱም በከተማ አካባቢ የሚገኙ ተማሪዎች በቀላሉ ሊያውቋቸው ባለመቻላቸው ነው። በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ውስጥ በትክክል ያካተተ መሆኑ ከትክክለኛነት አንጻር ጥሩ ገጽታ ያለው መሆኑን ለማየት ተችሏል።

### 4.4.3 ከተገቢነት አንጻር

በቋንቋመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ ቋንቋውን በሚማሩ ተማሪዎች አንጻር ታይቶ ተገቢነት ባለው መልኩ መቅረብ ይኖርባቸዋል። የትምህርቱ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ የሚቀርቡት ይዘቶቹ ወይም መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ የግንዛቤ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ዳራና የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ታይቶ ሊቀርቡ ይገባል። ከዚህ በመቀጠል በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ይዘትና መልመጃዎች ከተገቢነት አንጻር እንደሚከተለው እንመልከት።

በ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተማሪዎች አቅምና ችሎታ በላይ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አልተካተቱም ለማለት ይቻላል። ይዘቶቹም ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ስላለው ጥሩ የተገቢነት አቀራረብ እንዲኖረው አድርጎታል። በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ላይ የተገቢነት ችግር የለም። ነገር ግን በገጽ 80 ላይ ቃላት ከሚለው ስር የቀረበው የእርሻ መሳሪያ ስዕልና ስያሜውን ማዛመድ የሚለውን ከዚህ ቀጥለን እንመልከት።

የእርሻ መሳሪያ ክፍል ስያሜዎችን ከስዕሉ ጋር አዛምዱ ።

1.እረፍ 6. ማነቆ

2. ድግር 7. ቀምበር

3. ማረሻ 8. መዋጀ

4. ወገል 9. ምራን

5. መርገጥ 10. ሞፈር

ከላይ ያለውን ጥያቄ ስንመለከት የተገቢነት ችግር እንዳለበት ይታያል። ምክንያቱም እነዚህ ቃላቶች ወይም የእርሻ መሳሪያው ስያሜዎች እና እራሱ እርሻ መሳሪያው ከተማሪዎቹ ዳራና የክፍል ደረጃ ጋር ታይቶ በተገቢነት የቀረበ ባለመሆኑ ጥያቄው ከተገቢነት አንጻር ችግር ያለበት እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለማወቅ ተችሏል።

### 4.4.4 ከተመጣጣኝነት አንጻር

በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካተው የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሁሉም የቋንቋ ሰዋስዋዊ ክፍሎች የተውጣጡና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተመጥነው ሊቀርቡ ይገባል። በእርግጥ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ዘውትር የተመጣጠኑ ወይንም ሁሉንም የሰዋስው ክፍሎች በእኩል ደረጃ ለማቅረብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም በተቀራራቢ መጠን ብዙ ልዩነት ሳይኖር መቅረብ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ትኩረት የሆነው መማሪያ መጽሐፍ ከይዘት ተመጣጣኝነት አንጻር ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ይታያል። ተተኳሪው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከተመጣጣኝነት አንጻር ያለው ገጽታ እንደሚከተለው ተፈትሿል። በቅድሚ ስለመማሪያ መጽሐፉ የሰዋስው ይዘት ስርጭት ገጽታ በሠንጠረዥ መልክ እንመልከት

ሰንጠረዥ4.5፤-በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስርጭት

| ተ.ቁ. | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተካተቱበት ሁኔታ (መጠን) | |
|---|---|---|---|
| | | የሳምንታት ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | ስነ-ድምፅ | በ10 ሳምንታት | 33% |
| 2 | ስነ-ምዕላድ | በ18 ሳምንታት | 60% |
| 3 | ስነ-አገባብ | በ15 ሳምንታት | 50% |
| 4 | ስነ-ፍቺ | በ15 ሳምንታት | 50% |

ከሠንጠረዡ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ የተመጣጣኝነት ችግር በውስን ደረጃ እንዳለ ተስተውሏል። ይኸውም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች መካከል በከፍተኛ መጠን የተካተቱ ሶስት የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ናቸው። እነርሱም ስነ-ምዕላድ፣ ስነ-አገባብና ስነ-ፍች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉ ሳምንታትና ቀኖች ውስጥ በብዛት ተካተው ይገኛሉ። ነገር ግን ስነ-ድምፅ በ10 ሳምንታት ውስጥ ተካቶ ይገኛል። በመሆኑም በትምህርት ይዘቶቹ መካከል ያለው ልዩነት ተቀራራቢነቱ ጥሩ የሚባል ነው።

የስነ-ድምፅ ይዘቶችን በሚመለከት ከቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ውስጥ በደረጃው መጠነኛ ውስብስብነት ያላቸውን ድምፆችና ግንኙነት ይገነዘባሉ፤ በቃላት ውስጥ የሚካተቱ ድምፆችን (በገጽ 3፣ 9፣ 14፣ 34፣ 39፣) ያነባሉ፤ ድምፆችን በማጣመር (በገጽ 2፣ 3፣ 6፣ 8፣ 9፣ 14፣ 34፣ 39፣) ይጠቀማሉ የሚሉት ናቸው።

ስነ-ምዕላድን በተመለከተ ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በማጣመር፣ ቅጥያውን ከዋናው ቃል መነጠልየሚሉት በሚከተሉት ሳምንታት ገፆች ላይ ይገኛሉ። -2ኛ ሳምንት በገጽ 6፣ 7፣ -4ኛ ሳምንት በገጽ 15፣ 18፣ 19፣ -6ኛ ሳምንት በገጽ 23፣ 26፣ 27፣ 30፣ 34፣ -10ኛ ሳምንት በገጽ 38፣ -12ኛ ሳምንት በገጽ 48፣ -13ኛ ሳምንት በገጽ 51፣ 53፣ -20ኛ ሳምንት በገጽ 87፣ -21ኛ ሳምንት በገጽ 89፣ 91፣ -22ኛ ሳምንት በገጽ 94፣ 96፣ -24ኛ ሳምንት በገጽ 105፣ -25ኛ ሳምንት በገጽ 109፣ -26ኛ ሳምንት በገጽ 112፣ -27ኛ ሳምንት በገጽ 117፣ -28ኛ ሳምንት በገጽ 120፣ 122፣ -29ኛ ሳምንት በገጽ 125፣ 30ኛ ሳምንት በገጽ 129፣ እና 131 ላይ ተካቶ ይገኛል።

ስነ-አገብብን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በ3ኛ ደረጃ ተካቷል። በትምህርት ይዘቶች ስንመለከት የዓረፍተ ነገር ምስረታን በ1ኛ ሳምንት በገጽ 2፣4፣5፣ 6፣ 7፣ 11፣ 12፣ 16፣ 18፣ እና 24 ውስጥ ነው። የቃል ክፍሎችንና ሙያ ቀጥሎ የሚገኝ ሲሆን በ15ኛ ሳምንት በገጽ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 23፣ 25 እና 29 ላይ ሲሆን ዓረፍተ ነገርን ማስተካከል (በ8ኛ በ13ኛ፣ 19ኛ፣ 24ኛ፣) ሳምንታት እና ማሟላት (በ15ኛ፣ በ16ኛ፣በ18ኛና በ23ኛ) ሳምንታት ላይ ተካቷል።

ስነ-ፍችን በተመለከተ ከበፊት ከቀረቡት ጋር ተቀራራቢ በሆነ ደረጃ ላይ ነው። በመማሪያ መጽሐፉ ስነ-ፍችን በተመለከተ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥም ቃላትን ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ በ1ኛ፣ በ2ኛ፣ በ9ኛ፣ በ11ኛ፣ በ13ኛ፣ 16ኛ፣ በ17ኛ፣ በ21ኛ፣ በ22ኛ፣ በ24ኛ፣ በ26ኛ፣ በ27ኛ እና በ28ኛ ሳምታት ላይ

ተደጋግመው ሲገኙ የቃላት ተመሳሳይ ፍች በ5ኛ፣ በ9ኛ፣ በ14ኛ፣ በ15ኛ በ18ኛ፣ 22ኛ፣ በ25ኛ እና በ29ኛ ሳምነታት ላይ ሲካተት የቃላትና የሀረጋት አገባበዊ ፍች በ3ኛ፣ በ12ኛ፣ 13ኛ፣ በ15ኛ፣በ20ኛ ሳምንታት እና የቃላት ቀጥተኛ ፍች በ3ኛ፣ በ4ኛ እና በ14ኛ ሳምንታት ሲገኙ፣ የቃላትና የሀረጋት ተቃራኒ ፍች በ6ኛ፣ በ24ኛ እና በ29ኛ ሳምንታት ውስጥ ተካቷል።

በአጠቃላይ በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተመጣጣኝነትን በሚመለከት ተቀራራቢ የሆነ የሚዛናዊነት ችግር የሌለበት እንደሆነ ከተደረገው ሰነድ ፍተሻ ለመረዳት ተችሏል። በተደረገ የሰነድ ፍተሻ ተመጣጣኝነትን በተመለከተ የታየው ተቀራራቢነት በጣም ጥሩ የሆነና ሚዛናዊነቱን የጠበቀ መሆኑ ታይቷል።

## 4.5 የውጤት ማብራሪያ

በ2009 ዓ.ም. በታተመው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ሁኔታ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ለቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች ውጤት ተገኝቷል። የተገኘውም ውጤት ከምሁራን ሀሳብና ከሌሎች ቀደምት ጥናቶች አንጻር ታይቶ ተገልጿል።

ተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 30 ሳምንታትና 131 ገጾች ሲኖሩ ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርትም በሁለት ወሰነ ትምህርት ተከፍሎ ቀርቧል። በመማሪያ መጽሐፉና በመርሀ ትምህርቱ ውሰጥ እንደሌሎች የክፍል ደረጃዎች ለብቻው ሰዋስው ብሎ ባይቀርብም በውስጣቸው የሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ተደራጅተው ቀርበዋል።

ከዚህ አንጻር መማሪያ መጽሐፉ በደረጃው የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት መሰረት ተደርጎ በመዘጋጀቱጥሩ የሆነ ተጣጥሞሽ ያለው እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መካከል ጥሩ የሆነ የአደረጃጀትና አቀራረብ ሁኔታ እንዳለ በሚከተለው መልክ ለማየት ተችሏል።

በመሆኑም መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነት፣ ከመስመራዊና ኡደታዊ አደረጃጀት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር ተፈትሾ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ተከታታይነትን በተመለከተ የድግግሞሽ መጠን ስነ-ምዕላድ 18 (60%) በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ሰላሳ ሳምንታት ውስጥ በአስራ ስምንቱ ሳምንታት ውስጥ ተደጋግሞ በአንደኛ ደረጃ እናገኛለን። ስነ-ፍቺ 13 (43%) በሚመለከት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በአስራ ሶስቱ ሳምንታት በተደጋጋሚ በመቅረብ በሁለተኛ ደረጃ ይገኛል። በሶስተኛ ደረጃ ድግግሞሽ ያለው ስነ-አገባብ 10 (33%) እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለማወቅ ተችሏል። በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች መካከል በከፍተኛ መጠን የተካተቱ ሶስት የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች ናቸው። እነርሱም ስነ-ምዕላድ፣ ስነ-ፍችና ስነ-አገባብ በመጽሐፉ ውስጥ ባሉ ሳምንታትና ቀኖች ውስጥ በብዛት ተካተው ይገኛሉ። በመሆኑም በትምህርት ይዘቶቹ መካከል ያለው ልዩነት ተቀራራቢነቱ ጥሩ የሚባል ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ በመነሳትና በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተደረገው ፍተሻ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አንዱ ካንዱ የመበላለጥና የመጠጋጋት መጠኑ ተቀራራቢ በመሆኑ የተከታታይነት ችግር እንደሌለው ለማስተዋል ተችሏል።

ተለጣጣቂነትን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንጻር በስነ-ምዕላድ በኩል ያሉትን ይዘቶች ስንመለከት በዓይነትና በቅርፅ በመቀያየር በመደራጀቱ በተሻለ ሁኔታ ከሳምንት ሳምንት የሽግግር ተለጣጥቆነት የተሻለ እንደሆነ ተመላክቷል። እንዲሁም ስነ-ፍችን አስመልክቶ ተማሪዎቹ ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ፣ ለቃላቱ ፍቻቸውን እንዲፅፉ፣ ቃላት እንዲመሰርቱ እና ሆሄያትን በማጣመር ባለአራትና አምስት ፊደል ቃላት እንዲመሰርቱ በማድረግ የስነ-ፍችን አደረጃጀት ከሳምንት ሳምንት ከፍ እያለ ከቀላል ወደ ከባድ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ተለጣጣቂነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። ስነ-አገባብን አስመልክቶ ከቀረቡላቸው ቃላት ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ከማድረግ በመጀመር ተገቢ ስርዓተ ነጥብ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች እንዲፅፉና እንዲያነቡ እንዲሁም ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ተጠቅመው አንቀጽ ጽፈው እንዲያነቡ በማድረግ በየሳምንቱ ከቅለት ወደ ክብደት ደረጃ የመጡ መሆናቸው የተለጣጣቂነት ችግር የሌለባቸው መሆኑን ለማየት ተችሏል።

በአጠቃላይ በታላሚው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ክብደትና ስፋታቸውን እየጨመሩ የተደራጁ በመሆናቸው ተለጣታቂነት አላቸው።

መስመራዊ እና ኡደታዊ አደረጃጀትን በተመለከተ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ መስመራዊ እና ኡደታዊ አደረጃጀት ሁኔታ መኖሩን ከሰነድ ፍተሻው መገንዘብ ተችሏል። ይኸውም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ የንባብ ክሂል፣ የጽህፈት ክሂል፣ የንግግርና የስነጽሑፍ ይዘት ጋር አንዱ ሌላውን ለማስተማር ተግባር ተደራጅቶ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ የሰዋስው ይዘት እርስ በርሳቸው መስመራዊ እና ኡደታዊ ሂደትን ጠብቀው ዕድገት እያሳዩ አንዱ የሰዋስው ይዘት ሌላውን የሰዋስው ይዘት ዕድገት እንዲኖረው እየደገፈና እያዳበረ የመጣበት ሁኔታ እንዳለ ለማየት ተችሏል። ከዚህ በመነሳት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች ጋር እና እርስ በርስ ያላቸው ትስስር መስመራዊእናኡደታዊአደረጃጀት ጥሩ የሚባል እንደሆነ ከሰነድ ፍተሻው ለመረዳት ተችሏል።

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀትን በሚመለከት በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ በተደረገ ፍተሻ የሰዋስው ይዘቶችን አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከሚለው አደረጃጀት ስልት ጋር በጥምረት ተደራጅተው መገኘታቸውን ለመረዳት ተችሏል። እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፉ እና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በጣም የተጣጣሙና በዝግጅት ወቅትም ትኩረት ተሰቶት መርሀ ትምህርቱን መነሻ ተደርጎ መዘጋጀቱን ያሳያል።

በአጠቃላይ ብዙ ጠንካራ ጎን ቢታይበትም በመመሪያ መጽሃፉ በሳምንቶችና በቀናት ሲከፈል መርሀ ትምህርቱ በወሰነ ትምህርት ብቻ መከፈሉ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጠንካራ የሆነ ትስስርና ዝምድና እንዳላቸው የተደረገው የሰነድ ፍተሻ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉና ለደረጃው በተዘጋጀው መርሀ ትምህርቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ከተሰጠው ትኩረት አንጻር ተደራጅቶ መገኘቱን ከሰነድ ፍተሻው ለማረጋገጥ ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋነኛ ዓላማ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የተዘጋጀው የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል እና መማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ሲሆን በዚህ ዓብይ ዓላማ ስር የሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

1. መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል፣
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀታቸው ምን ይመስላል
3. የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ተጣጥሞሽ አለው ወይ የሚሉት ናቸው።

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሰነድ ፍተሻው የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ካስገኙት ውጤት መረዳት የተቻለው በተተኳረው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ጠንካራ ጎን ያለው መሆኑን ተስተውሏል። ነገር ግን ጥቂት ድክመት እንዳለው ለማየት ተችሏል። በመቀጠል ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶችም ተጠቃለው ይቀርባሉ።

የ3ኛ ክፍል አማርኛን እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋስው ትምህርት ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች አንጻር ሲታይ በቂ ቦታ እንደተሰጠው ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ሲታይ ተከታታይነቱ ከቀላል ወደ ከባድ የሄደና ተለጣጣቂነቱም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ለተማሪዎቹ የሚመጥን መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

በሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ስንመለከት በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከግልጽነት፣ ከምሳሌዎችና ከመልመጃዎች አኳያ ዘጠና ሰባት በመቶ በላይ ችግር የሌለባቸው ሆነው ቀርበዋል። ይሁን እንጂ ጥቂት መልመጃዎች ከትዕዛዞች አቀራረብ ላይ መጠነኛ ድክመት እንዳለበት ለመረዳት ተችሏል። ሌላው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ሲቀርብ ከተገቢነት አንጻር ሲታይ ዘጠና ሰባት በመቶ በላይ መልመጃዎች የቀረቡላቸው ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ የግንዛቤ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ዳራና የክፍል ደረጃ ጋር የሚመጥኑ መልመጃዎች እንደተመረጡ መገንዘብ ተችሏል። ይሁን እንጂ ከዳራቸው ውጪ የገቡ የሰዋስው ይዘት ያላቸው ከሶስት በመቶ በታች ቃላትና ሀረጋት መቅረባቸው ተስተውሏል።

በመጨረሻም መማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ በተመለከተ ጥሩ የሚባል ቢሆንም መማሪያ መጽሐፉም ሆነ የደረጃው መርሀ ትምህርት በምዕራፍና በጊዜ አለመከፋፈሉ እንደ ድክመት ለማየት ተችሏል።

## 5.2. አስተያየት

ከላይ በማጠቃለያው በተገለጹት የጥናት ውጤት መሰረትበማድረግ መጽሐፉ ብዙ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት የሚታወቅ ቢሆንም የታዩትን ችግሮች ወደፊት ለሚዘጋጁ የ3ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የይዘት አመራረጥና አቀራረብ እንዲሁም ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ለመፈተሽያስችሉ ዘንድ አጥኚዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርባለች።

1. መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ መቅረባቸው ጥሩ ቢሆንም ስለ ሰዋስው ይዘቶች እንዲያውቁ ተገቢው ትኩረት ቢሰጥ።
2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በአብዛኛው የቀረቡት ምንባቦች ናቸው። ከምንባቦቹ በተጨማሪም ወደፊት በሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ላይ ለደረጃው የሚመጥኑ ማስታወሻዎች ቢቀርቡ፤
3. በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ አዳዲስና ያልተለመዱ ወይም ለደረጃው እንግዳ የሆኑ ሰዋስዋዊ ቃላትና ሐረጋትን ሲከሰቱ ተማሪዎች እንዳይደናገሩ አቅጣጫ የሚጠቁምና ፍች የሚሰጥበት ክፍል ቢኖር፤

4. መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ ተጣጥመው መቅረባቸው ጠንካራ ጎኑ ቢሆንም በምዕራፍ እና በክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ተከፋፍሎ ቢቀርብ፤

5. አጠቃላይ በሆነው የመማሪያ መጽሐፉ ገጽታ በስርዓት የተደራጀና ቅደም ተከተል የጠበቀ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ፤ ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ የተደራጀ በመሆኑ ቀጣይ በሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ላይም ቢደገም ጥሩ ይሆናል።

# ዋቢ ጽሑፎች


ባየ ይማም፡ 2009። የአማርኛ ሰዋሰው፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቢ.ኢ. ማተሚያ ቤት።

ባየ ይማም፡ 2004። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋሰው። (3ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፤አልፋ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ሸዋዬ፡ 1981። ስነ ልሳንና ቋንቋ ማስተማር። አዲስ አበባ(ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቅ። 2009። የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር። (3ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። 2011። የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ። (2ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቢ. ኢ. ማተሚያ ቤት።

Cunning S.worth, A. (1984).Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials (5th print).Oxfored; Heinman.

Dubin, F. and E, Olshtatia.(1986). Course Design.Cambridge; Unversity.

Larson-Freeman, D. (1986). Techniques and Principles in language teaching.Oxfored university press.

Ur, P. (1988). Grammer practice Activities. Cambridge; university press.

Brown,K.et.al.(2006). Languadge and linguistics. (2nd ed) Encyiclopedia vol.g Oxfored; Elsevier Ltd.

Bygate, M et. al. (1994).Grammer and the languadge Teacher. Hemposted PrenticeHall.

Grant, N. (1988). Making The most of Your Text Book.Longman group.

Harmer,J. (1987). Teaching and Learning Grammer.London; Longman.

Richards. J. and Rodgers T. (1986). Approaches and Methods in Languadge Teaching Cambridge;Cambridge Unversity Press.

Stem, H. H. (1992). Issues and Options in Languadge Teaching.Oxfored Unversity Press.

Swan, M. (!994). ”Design Criteria for pedagogic Languadge Rule” in Bygate, M, etal. Grammer and The Languadge Teachers. Newyork prentia Hall.